# ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፡፡

# Ethiopia: The Kingdom of God Services

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳት፥ የ"ኢትዮጵያ" እና "የኢትዮጵያውያን" የኾነውንም ኹሉ ለመጠበቅና ለማሳወቅ፡፡
To reveal the truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God; and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.

በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ፡ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤
በስማ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤
በኃይለ መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

## "ጾመ ኢትዮጵያ"

## "ኢትዮጵያዊዉን ችግር"፡ በ"ኢትዮጵያኛው መላ" ለማስወገድ፡፡

## የዘ ድሮውን መልእክት፡ የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!

ተጻፈ፡ በጾመ ማርያም፤ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን፥ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ይድረስ፡-

በኢትዮጵያ ላላችሁትና በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥ በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥ በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥ በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ! ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም! ለአዛውንቱም፥ ለወጣቱም! በየግላችሁም! ለኹላችሁም!

እኔ፡ የኢትዮጵያ አገልጋይ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን፡ በያላችሁበት አቀርብላችኋለሁ፡፡

በአኹኑ ጊዜ፡ ተስፋፍቶና ሥር ሰድዶ ያለው፡ ኢትዮጵያዊው ችግር፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ተሠውሮ ኖሮ፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ከተከሠተ በኋላ፡ እነሆ፡ ከሠላሳ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ እስከዛሬ ቀጥሎ ይገኛል፤ ይህንኑ ችግር፡ በሰውኛው ብልሃትና ጥበብ፥ ኃይልና ገንዘብ ለመፍታት፡ አያሌ ሙከራና ብርቱ ጥረት ቢደረግም፡ እየበረታ ከመኼድ በቀር፡ ለማቃለልና ለማስታገሥም እንኳ፡ ፈጽሞ አልተቻለም፤ ይህንም፡ ይኸው፡ እኛ ራሳችን፡ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንኾን፡ መላው ዓለም ጭምር፡ በገሃድ ይመለከተዋል፡፡

እውነታው፡ ይኼ ከኾነ ዘንድ፡ ታዲያ! ይህን ኢትዮጵያዊ ችግር፡ ለመፍታትና ለማስወገድ የሚቻለው፡ እንዴት ነው? ሌላ፡ ምን ዓይነት አማራጭ ዘዴ አለን? ከሌለንስ፡ "የለንም!" በማለት፡ ዝም ብለን ልንቀመጥ፥ ወይም፡ ልንመለከት ይገባናልን? አይደለም! ለፈጣሪያችን፡ ምስጋና ይድረሰውና! በሌላኛው፥ በሰውኛው መንገድ፡ የማይቻለው ኹሉ፡ በእኛ ዘንድ እንዲቻል ስላደረገው፡ እኛ፡ ኢትዮጵያውያንማ፡ እንዲህ አንልም፡፡

…፪

መልእ. ሣ. ቁ. ፰፻፲፪፤ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፰-፹፭፤ ፳--፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ፡፡
P. O. Box 812, Tel. Nos. 16-18-85; 20-00-85, Addis Abeba, Ethiopia.
P.O.Box 43262, Washington, DC 20010-9262 U.S.A.
Tel. (301) 587-8074 ~ Fax: 301-587-1971 ~ E-mail: ekogyesus@aol.com
Website: www.ethkogserv.org

እንግዴህ፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ችግራችንን፡ እንዴት አድርገን፡ በቀላሉና በፍጥነት፥ በጸጥታና በወግ ለመፍታትና ለማስወገድ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ክፉው ጊዜ አልፎ፡ የምንመኘው፡ ደጉና ደኅናው፥ የሰላሙና የብልጽግናው ዘመን፡ በቶሎ እንዲመጣ ለማድረግ እንደምንችል፡ እኔ አመለክታችሁ ዘንድ፡ እስኪ፡ ፍቀዱልኝ!? ይህን ችሮታ የምጠይቃችሁ፡ እስከዛሬ፡ ለባዕዳኑ፥ ለተቃዋሚዎቻችን ሳይቀር፡ አለቁጥጥር፡ ልቅ አድርጋችሁና አትረፍርፋችሁ የለገሣችሁትን ፈቃዳችሁን፡ አኹን፡ ለእኔ፡ ለወገናችሁ፡ ቆጥባችሁም ቢኾን፡ ለአንዴ ለመስጠት፡ ምንም ቢኾን፡ "አትነፍጉኝም!" ብዬ በማመን ነው፤ ይህንም በማድረጋችሁ፡ የአገራችሁንና የወገናችሁን፥ የየራሳችሁንም ደኅንነት፡ የቱን ያህል እንደጠቀማችሁ፡ የኋላ ኋላ፡ ታስተውሉታላችሁ። በዚህ መልክ፡ ፈቃዳችሁን ካገኘሁ፡ ለዚሁ፡ ለኢትዮጵያዊው ችግራችን፡ እኔ፡ የማቀርብላችሁ የመፍትሔ አሳብ፡ "ያገሩን ሠርዶ፡ ባገሩ በሬ!" እንዲሉ፡ በዘበናዮች ዘንድ የተናቀውን፡ "ኢትዮጵያኛውን መላ" መኾኑን ሳበሥርላችሁ፡ ደስ ይለኛል።

"ኢትዮጵያኛው መላ" ያልሁትም፡ በይፋ ታውቆ የ ረውንና የባዕዳኑ ፈሊጥ፡ በምንም ዓይነት ያልተቀላቀለበትን፥ ፍጹም ንጹሕና አገር-በቀል የኾነውን እንጂ፡ አዲስ፥ ወይም፡ እንግዳ የኾነውን አይደለም፤ ኢትዮጵያውያን፡ ከጥንት ጀምረው፡ ለአያሌ ሺህ ዓመታት፡ እንደዛሬው ዘመን፡ በግልም ኾነ፡ በአገር ደረጃ፡ ማናቸውም ዓይነት ችግር ሲገጥማቸው፡ ያን ችግር፡ ፈትተው፡ እያስወገዱ የ ሩበትን ማለቴ ነው፤ ይኸው ችግር፡ በአኹኑ የኢትዮጵያ ትውልድና በባዕዳኑ ሰዎች ዘንድ፡ እንዲህ፡ መፍትሔ ያጣና ግራ የሚያጋባ፥ በምሥጢር የተተበተበም በሚኾንባቸው ጊዜ፡ የተጠቀሙበትን፥ ዛሬም፡ ፈትተው፡ ሊያስወግዱ የሚችሉበትን፡ ልዩ የብልህነት ዘዴያቸውን ነው፡ እኔ፡ "ኢትዮጵያኛው መላ" ያልሁት።

በመሠረቱ፡ "ችግር" የሚባለው፡ የሕይወት ጠንቀኛ ጣጣ፡ እንደክፉት፥ እንደኃጢኣትና እንደሞት ኹሉ፡ በራሱ፡ በሰው ፍላጎት የመጣ እንጂ፡ ጥንት፡ በተፈጥሮ፡ የህልውና አካል ኖሮት፡ የተከሠተ ኾኖ አይደለም፤ ቀድሞውኑም ቢኾን፡ ችግርን፡ ፈልጎ ያመጣው፡ ከቀዳማዊው አዳም ጀምሮ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ ራሱ ሰው መኾኑ ተጽፏል፤ ይታወቃልም፤ ያው ሰው ደግሞ፡ ሲፈልግ፡ ያንኑ፡ ፈልጎ ያመጣውን ችግር፡ ራሱ መልሶ ሊያስወግደው ችሎ እንዳስወገደው፥ ለኹልጊዜም ሊያስወግደው እንደሚችል፡ ከዳግማዊው አዳም፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ፡ በእርሱ በተፈጸመው ቤዛነትና ለቀረው ሰው ኹሉ በተሰጠው ጸጋ፡ እስከዛሬና ለዘለዓለም፡ የተረጋገጠ እውነታ ኾኗል። ከዚህ የተነሣ፡ በአኹኑ ጊዜ የተንሰራፋውን ኢትዮጵያዊ ችግር፡ ፈልጎ ያመጣው፡ ራሱ፡ ይህ፡ ኢትዮጵያዊ ትውልድ እንደመኾኑ መጠን፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ ከፈለገ ደግሞ፡ ይህንኑ፡ ከዓቅሙ በላይ የኾነበትንና በሰውኛው ዘዴ ሊያስወግደው ያልቻለውን፡ ኢትዮጵያዊ ችግሩን፡ ራሱ፡ መልሶ፡ ሊያስወግደው እንደሚችል፡ ሊገነዘበው ይገባል። አዎን! የሚያስወግደውም፡ በ"ኢትዮጵያኛው መላ" ብቻ ነው።

የፍጡር አካል፡ በሥጋው፡ ሕያው ኾኖ ሊንቀሳቀስ፥ ሊሠራና ሊኖር የሚችለው፡ በነፍስ፡ የኃይል ምንጭነት መኾኑ፥ ደግሞም፡ ሰው የሠራው ሠረገላ እንኳ፡ በመንቀሳቀስ ሊያገለግል የሚችለው፡ በዚያው፡ በሠሪው፡ በሰው ተቆጣጣሪነት መኾኑ ይታወቃል። እንደዚሁ ኹሉ፡ አንድን ግለሰብ፥ አንድን ቤተሰብ፥ አንድን ኅብረተሰብ፥ ወይም፡ አንድን ሕዝብ፡ አስማምቶና አዋሕዶ የሚያኖረው፥ የሚያንቀሳቅሰውና የሚያሠራው፡ አንድ ኃይል ሊኖረው፡ የግድ ያስፈልጋል፤ ሌላ አማራጭ የለም፤ አለዚያ፡ ያ ግለሰብ፥ ያ ቤተሰብ፥ ያ ኅብረተሰብ፥ ወይም፡ ያ ሕዝብ፡ ሕያው የኾነ፡ ህልውናን አግኝቶ፡ በዚያ ሕይወት ሊቀጥል አይችልም። ያም ኃይል፡ ሃይማኖት ነው። የዚያ አካል፡ ህልውናው፡ መልካምና ፍሬያማ እንዲኾንለት ከተፈለገ ደግሞ፡ ያ ሃይማኖት፡ ፍጹም ንጹሕና እውነት መኾን ይኖርበታል።

ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ ለህልውናቸው፡ ታላቅ አገልግሎትን ያበረከተላቸው ኃይል፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው መኾኑን ለማስተባበል፡ አይቻልም፤ እርሱም፡ በፍቱን መሣሪያነቱ፡ ለችግራቸው ማስወገጃ አድርገው ለሚጠቀሙበት፡ ለ"ኢትዮጵያኛው መላ" ጥሩ ምንጭ ኾኗቸው ኖርዋል። ነጻነታቸውን በማስገኘቱ፥ ይህንኑም ነጻነት፡ ለ፯ሺ፬፻፺፰ ዓመታት አጽንቶና አረጋግጦ፡ እስከዛሬ በማቆየቱ ረገድ፡ ሙሉና የብቻው የኾነ ድርሻ ያለው፡ ይኸው ሃይማኖታቸው ነው፤ ለዚህም፡ እንደዐለት ድንጋይ ጸንቶና ነዋሪ ኾኖ ከሚመሰክረው፡ ከራሱ ሐውልትነት የበለጠ፡ ሌላ ማስረጃ አያስፈልገውም።

…፫

እንዲህ ከኾነ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ እስከዛሬ የ ረውን፥ በሕያውነቱም፡ ለዘለዓለም የሚቀጥለውን፡ ይህን የመሰለውን ፍቱን መሣሪያ፡ የዘመኑ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በጊዜው ለተጋረጠበት ኢትዮጵያዊ ችግር ማስወገጃ አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚገባ፡ እሙን ነው፡፡ ነገር ግን፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ ለመልካምና ለዘለቄታ ህልውናው፡ መሠረትና ማንቀሳቀሻ የኾነውን፡ ይህን ፍቱን ኃይል፡ መሣሪያ አድርጎ ሊጠቀምበት አልፈለገም፤ ባለመፈልጉም፡ እነሆ፡ ችግሩ፡ እየጸናበት ከመኼድ በቀር፡ የተሻለ ነገር ሊመጣለት የማይቻል ኾኖ ቆየ፡፡ የዚህን እውነታ ለማረጋገጥ፡ ወደሩቅ ዘመን መኼድ ሳያስፈልግ፡ እስከዛሬ፡ ከሰላሣ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን የቀጠለውንና እየባሰ የኼደውን፡ ይህንኑ ችግር፡ በተጨማሪ ማስረጃነት ማቅረቡ ብቻ የሚበቃ ይኾናል፡፡

"ኢትዮጵያኛውን መላ" ከመግለጼ በፊት፡ ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ችግር፡ ብዙዎችን የእውነት ሰዎች ሳይቀር፡ አሳዝ ፡ ተስፋ ወደማስቆረጡና እስከማስለቀስ ማድረሱን በተመለከትሁ ቊጥር፡ ገለጥ አድርጌ በማንበብ፡ እኔ የምጠናከርበት፡ አንድ መጽሐፍ መኖሩን ልገልጽላችሁ እወድዳለሁ፤ እርሱም፡ ዓለም የተቀበለው፡ ገናናው የእውነት መጽሐፍ ነው፤ በዚያ የተመዘገበውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የባለራእዩን ቃል፡ እናንተም፡ እንደምትጽናኑበት በማመን፡ እዚህ ላይ፡ አስቀድሜ እጠቅስላችሁ ዘንድ አግባብ ኾኖ አገኘሁት፡-

> "በውስጥና በውጭ የተጻፈባት፥ በሰባት ማኅተም የታተመች መጽሐፍ፡ በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ተይዛ፥ ታላቅ መልአክም፡ 'ያችን መጽሐፍ ሊከፍት፥ ማኅተሟንም ሊፈታ፡ የሚገባው ማነው?" እያለ፡ በታላቅ ድምፅ ሲያውጅ አየሁ፡፡ ያችን መጽሐፍ ለመክፈት፥ ለማየትም የተቻለው፡ በሰማይም ቢኾን፥ በምድርም ቢኾን፡ ማንም አልተገኘም፡፡ ያችን መጽሐፍ፡ ሊከፍታት፥ ሊያያትም የሚገባው፡ ማንም ስላልተገኘ፡ ብዙዎች አለቀሱ፤ እኔም አብሬአቸው አለቀስሁ፡፡
>
> "በእዚያ ከነበሩት አለቆች መካከል፡ አንዱ፡ እንዲህ አለኝ፡- 'ኢትብኪ! ናሁ፡ <u>ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ</u>፥ ዘእምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፥ ከመ ይፍትሓ ለይእቲ መጽሓፍ፥ ወለማኅተሚሃ!'" ይህም "'አታልቅስ! እነሆ፡ ከዳዊት ሥር፥ ከይሁዳ ወገን የኾነ አንበሳ፡ ይህችን መጽሐፍ ይገልጥ ዘንድ፥ ማኅተሟንም ይከፍት ዘንድ፡ ድል ነሥቷል!'" ማለት ነው፡፡ (ራእ. ፭፥ ፩-፭፡፡)

በዚህ ቃል መሠረት፡ "ችግር"፡ ከእግዚአብሔር አብና ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ድል አድራጊነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ተፈትቶ ተወግዷል፤ እንዲህ ኾኖ መወገዱን አረጋግጠን ካወቅን፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ከእኛ፡ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀው ድርሻ፡ ተስፋ በመቊረጥ፡ ማልቀስ ሳይኾን፡ በዚህ ዜና፡ ደስ ተሰኝተን፡ ባገኘነው ጸጋ፡ የየግል ግዳጃችንን ለመፈጸም መዘጋጀት ነው፡፡ የዚህ ዝግጅታችን፡ መነሻና መድረሻ፡ ምን እንደኾነ፥ እንዴትስ፡ መካኼድና መከናወን እንዳለበት፡ ላመልክታችሁ!

በረቂቅ ኃያልነቱና በፍቱን መሣሪያነቱ የሚታወቀው፡ "ኢትዮጵያኛው መላ"፡ ለኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው አማካይነት፡ ከፈጣሪያቸው የተሰጣቸው፡ ልዩ ጸጋ ነው፤ ሌላ ማማረጫ ሳያስፈልገውም፡ ከዚህ ዘመን ደርሷል፤ እርሱንም፡ ኢትዮጵያውያን፡ በማሰብ፥ በመናገርና በማድረግ ሲጠቀሙበት፥ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስም ሲፈጽሙት፡ እስከዛሬ ኖረዋል፡፡ ታዲያ! ለኢትዮጵያውያን፡ የመፍትሔ ኃይል ያለውና ረቂቅ መሣሪያቸው የኾነው፡ ይህ፡ "ኢትዮጵያኛው መላ" ከቶ ምንድር ነው? "ኢትዮጵያኛው መላ"ማ፡ በ<u>"ጾመ ኢትዮጵያ"</u> የተከሠተው፡ ሃይማኖታዊው ምግባራቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን፡ ሥጋዊ ዓቅማቸው በሚፈቅድላቸው መጠን፡ ለሦስት ቀናት፡ በጽሙና የሚጠመዱበት፡ የ ስሓ ጾም፥ ጸሎትና ምጽዋት ነው፡፡ "ጾመ ነነዌ" እያልን፡ በያመቱ፡ በልማድ ብቻ ስንጾማት የ ርነውን፡ የሦስት ቀኖች ጾማችንን፡ እንዳለፉት ዓመታት፡ ዘንድሮም፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" ብለን፡ እንጾማት ዘንድ፡ አገራችን፡ በስሟ ያቀረበችልን፡ ታላቁ ጥሪዋ ነው፡፡ ሲጠራቀምና ሲከማች ኖሮ፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የፈነዳውን፥ ከየራሳችንም የጀመረውን፡ ይህን፡ የዛሬውን፡ አገራዊና ሕዝባዊ ችግራችንን ለማስወገድ እንዲያስችል፡ መልካም አጋጣሚ ኾኖ፡ ለኢትዮጵያውያን የቀረበው፡ <u>"ጾመ ኢትዮጵያ"</u> ነው፡፡

አዎን! ስለአገራችንና ስለእየራሳችን፥ ስለወገኖቻችንና ስለዓለሙም፡ በተለየ ሃይማኖታዊ ትኵረትና መንፈሳዊ ተመስጦ ተዘጋጅተን፡ በግልና በኅብረት ልንጸማት የሚገባን፡ የኢትዮጵያ ጾም ናት፡ ይህች፡ የ"ኢትዮጵያኛው መላ" ፍቱን ኃይልና መሣሪያ።

እንግዲህ፡ አገራችን ኢትዮጵያ፡ በስሟ ያቀረበችልንን፡ ይህን ታላቅና ልዩ ጥሪ፡ በሙሉ ፈቃድ የምንቀበለው ከኾነ፡ ይህ መልእክት፡ በማናቸውም መንገድ፡ ከእያንዳንዳችሁ ጆሮ፥ ወይም፡ እጅ፡ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ፥ በተለይም፡ በመጨረሻ፡ <u>ከሰኞ፡ የካቲት ፮ እስከረቡዕ፡ ፰ ቀን፥ ፲፱፻፺፰ ዓ. ም.</u> ባሉት ሦስት ቀኖች ውስጥ፡ በምግባር ላይ ውሎ፡ እስከሚፈጸምበት ዕለት ድረስ፡ የ"ጾመ ኢትዮጵያ"ን ሥርዓት፡ በንጹሕ ኢትዮጵያዊነታችን ተከትለን፡ ለመልካሙ ፍሬ እናበቃው ዘንድ አሳስባችኋለሁ።

ይህ ሥርዓት፡ አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ በየቤታቸው ተወስነው፥ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ጫማቸውን አውልቀው፥ ከአልጋ ወርደውና ተለይተው፥ በምድርም ላይ ወድቀው፥ እየራሳቸውን፡ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊ መንፈስ አንጽተውና አጽንተው፥ ኹሉን በሚያውቀው ፈጣሪያቸው ፊት፡ የውጭና የውስጥ ኹለንተናቸውን ገላልጠው የሚያቀርቡበት ነው። እኛ፡ የዛሬዎቹ ልጆቻቸው፡ የእነርሱን ፈለግ በመከተል፡ እያንዳንዳችን፡ በያለንበትና በየተግባራችን ተወስነን፥ በቀናች ሃይማኖትና በትክክለኛው ምግባር ተጠምደንም፡ በቅድሚያ፡ እየራሳችንን፡ ከራሳችን፥ ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር፡ በንስሓ የምናስታርቅበት ነው። ቀጥለንም፡ በየግል ሰውነታችንና እርስ በርሳችን፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ አንድ ኾነን፡ ከፈጣሪያችን ጋር፡ በእውነተኛው አምልኮ የምንገናኝበት ነው።

ይህን ካደረግን፡ እኛ፡ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን፡ ከየራሳችንና ከአምላካችን፥ ከወገናችንም የሚፈለግብንን የመጨረሻ ግዳጅ መፈጸማችን ነውና፡ ለዛሬው ችግራችን፡ መፍትሔ የሚኾነንን ምሕረት፡ በእርግጥ፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪያችን እናገኛለን፤ ማግኘታችንንም፡ ከእርሱ ወርዶ የሚያድርብንና ኹሉን የሚገልጽልን፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ፡ ራሱ፡ ያሳውቀናል፤ "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!" የሚለውን መለኮታዊ መመሪያችንን፡ በሥራ ላይ ማዋላችንንም፡ ያስረዳናል፤ የኢትዮጵያኛው መላችን አካላት የኾኑትን፡ እነዚህን፡ ጾምን፥ ጸሎትንና ምጽዋትን፡ አጠቃልሎ የያዘውን፡ ሃይማኖታዊ ምግባራችንን፡ ለንስሓ ፍሬ ማብቃታችንን ያበሥረናል፤ በፍጻሜውም፡ ይህን የምንሻውን መለኮታዊ ምሕረት፡ በግልና በአገር ደረጃ፡ ለእኛ ብቻ ሳይኾን፡ ከዚያም አልፈን፡ ለዓለሙም ጭምር፡ በሚያስተማምን መልኩ ለማስገኘት መቻላችንንም ያስገነዝበናል።

ከሦስቱ ቀኖች ጾማችን፡ የሚጠበቀው ፍሬያማ ውጤት የሚገኘው፡ ከላይ የተጠቀሱት ዕለታት ደርሰው፡ ሱባኤው በሚፈጸምበት ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን፡ ገና ከወዲሁ፡ የዚህ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ሰልፍ ዝግጅት፡ ዜናው መሠራጨት ጀምሮ፡ መልእክቱ፡ ከእያንዳንዳችሁ ጆሮ ሲደርስ፡ ውጤቱን፡ በአንዳንድ ምልክቶች ተከሥቶ ታገኙታላችሁ። ከእነዚህም ምልክቶች መካከል አንዱ፡ የዚህ ችግራችን ክፉ ምንጭና አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ፡ ከነሠራዊቱ፡ ማለትም፡ አጋንንቱንና ሰብአውያን አገልጋዮቹን ጨምሮ፡ በመበርገግ፡ ከሚደርስበት ጭንቀትና ጥበት የተነሣ፡ የሚያደርገው መወራጨትና መታወክ ነው። በዚህ ጊዜና በዚህ አንጻር፡ በእኛ በኩል፡ ሊታይ የሚገባው፡ በጎ ምልክት ደግሞ፡ በእግዚአብሔር መንፈስና በእውነተኛ አምልኮ ኾነን በምንፈጽመው በዚህ ጾማችን ምክንያት፡ በውስጣችን የሚሰማን፡ መታመንና በውጫችን የምናሳየው፡ እርጋታ ይኾናል።

በአኹኑ ጊዜ የተከሠተውና የተፈጸመው፡ ይህ፡ የ"ጾመ ነነዌ" እና የ"ጾመ ኢትዮጵያ" ጥምረትና ትሥሥር፡ በሥራ ላይ እንዲውል የኾነው፡ ያለምክንያት አይምሰላችሁ፤ በመጨረሻው ዘመን፡ ከፍጥረተ ዓለሙ ጋር ሊፋረዱ፡ በእግዚአብሔር ችሎት ፊት የሚቀርቡት፡ የነነዌ ሰዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ በመኾናቸው ነው፤ የነነዌ ሰዎች፡ በነቢዩ ዮናስ ስብከት፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛ ንስሓ በማብቃታቸው፡ የፈጣሪን ምሕረት አግኝተው፡ ከመደምሰስ ድነዋል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፡ አምላካቸው እግዚአብሔር፡ ለሰሎሞን የሰጠውን የጥበብ ጸጋ፡ በዝ ስለሰሙ፡ ያንን ዜና፡ በዓይኖቿ አይታና አረጋግጣ ትመለስ ዘንድ፡ ንግሥታቸው ማክዳ፡ ከአገራቸው፡ ከኢትዮጵያ ምድር ተነሥታ፡ ወደኢየሩሳሌም እንድትጓዝ አድርገዋል። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለውን፡ የዚህን ዝክረ ነገር የሚያወሳውን ቃል፡ እዚህ ላይ ልጠቅስላችሁ፡ አግባብ ይኾናልና፡ ስሙት፡-

...፭

“ከጻፎችና ከፈሪሳውያን መካከል፡ ሰዎች መጥተው፡ 'መምህር ሆይ! ከአንተ፡ ምልክት ልናይ እንወድዳለን፤' አሉት። ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡ 'ከዳተኛዪቱ፥ ዓመፀኛዪቱና አመንዝራዪቱ ትውልድ፡ ምልክትን ትሻለች፤ ነገር ግን፡ ከነቢዩ፡ ከዮናስ ምልክት በቀር፡ ምልክት አይሰጣትም። ...የነነዌ ሰዎች፡ በፍርድ ቀን ተነሥተው፡ ይህችን ትውልድ ይፋረዷታል፤ ያሳፍሩዋታልም፤ በዮናስ ስብከት፡ ንስሓ ገብተዋልና፤ እነሆ፡ ከዮናስ የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ። ንግሥተ አዜብ፡ በፍርድ ቀን ተነሥታ፡ ከዚች ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፤ ታሳፍራታለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ፡ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።'”

(ማቴ. ፲፪፥ ፴፰-፵፪።)

ከዮናስና ከሰሎሞን የሚበልጠው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን፡ ይህን መለኮታዊ እውነታ፡ ለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድና ለዓለሙ ኅብረተሰብ ለማረጋገጥ፡ ወደሩቁ የዜና መዋዕል መዝገብ፡ ተመልሶ ኼዶ መመራመር አያስፈልግም፤ የቅርቡን፡ የኹለተኛውን የዓለም ጦርነት ዝክረ ነገር፡ አገላብጦ ማዘከር ይበቃል፤ አዎን! የዚያን ጊዜዎቹ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ መሪዎችና የዓለሙ ኃያላን መንግሥታት፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ ኢትዮጵያን፡ ማን እንደኾነች፡ ጥሩ አድርገው ያውቋታል፤ የሀብቷና የጥበቧ፥ የኃይሏም ምንጭ በኾነው በፈጣሪዋ፡ ከመተማመን በቀር፡ ያለማረሻ፡ ምንም ነፍጥ (የሚተኮስ ጦር መሣሪያ) የሌላት፥ የእግዚአብሔርና የቅድስት እናቱ ስም፡ የሚቀደስባት፥ መንግሥቱ፡ በይፋ የሰፈነባትና የቃል ኪዳን ቅርሶቹ፡ የሚጠበቁባት፥ ሕዝቡም፡ በትንሹ፡ “በቃኝ!” ብሎ፡ በመንፈሳዊ ትሕትና የሚኖርባት መኾኗን፡ ለራሳቸው ተገንዝበው፡ ለሌላውም ጽፈው ያስረዳሉ። ይኹን እንጂ፡ በዚያን ጊዜ፡ እርሷን፡ ለዘር ጠላቷ፡ በክህደት አሳልፈው በመስጠት አፈራርሰው፡ እነርሱ፡ በሰላም የሚኖሩ መስሏቸው፡ በኢትዮጵያ ላይ በፈጸሙት ታላቅ በደል፡ እኒያ መሪዎችና ኃያላን፡ ከነቃል ኪዳናቸውና የመንግሥታት ማኅበራቸው ጋር፡ የደረሰባቸው ፍጻሜ፥ አዎን! ለዚያ ደባቸውና ክህደታቸው፡ በናዚ ጀርመን፥ በፋሺስት ኢጣልያና በተስፋፊዋ ጃፓን አምባገነን ጦረኞች፡ የተከፈላቸው የፍርድ፥ የበቀልና የቅጣት ዋጋ አይዘነጋም።

እነዚያ ኃያላን፡ ዛሬም እንደገና፡ የዘመኑን፡ የኢትዮጵያ ትውልድ መሪዎችና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታቸውን ይዘው፡ የቀድሞውን የመሰለ ደባቸውን፡ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ፡ ያለኃፍረትና ያለይሉኝታ ሲያካኺዱ፡ ይኸው ይታያል። ይኹን እንጂ፡ ይህ ክፉ ግብራቸው፡ እንደዚያን ጊዜው ኹሉ፡ በመለኮታዊው ነደ እሳት ለመጫወት እንደመሞከር የሚያስቆጥራቸው መኾኑን አስተውለው፡ ከዚህ ድርጊታቸው ይታቀቡ ዘንድ፡ ያለፈው ዝክረ ነገር፡ የማስጠንቀቂያ ደወሉን በማሰማት፡ እነሆ፡ እነርሱንም፥ የዛሬውን የኢትዮጵያ ትውልድም፡ ያለማሠለስ፡ ያሳስባቸዋል፤ ነገር ግን፡ ኹሉም፡ ደወሉን ያዳመጡት አይመስልም፤ ባለፈው ጊዜ፡ ከታላቁ የእውነት ዳኛ፡ በየድርሻቸው የተሰጣቸው የፍርድ ጽዋ፡ ትምህርት ኾኗቸው፡ ካኹኑ ጥፋታቸው ተጸጽተው፡ ሊመለሱ አልተቻላቸውምና።

ለ“ጾመ ኢትዮጵያ”፡ መነሻ የኾነውም፡ ይህ፡ አደገኛ ኹኔታቸው ነው። እየራሳቸውን፡ ከባሰ ቅጣት ለማዳን ሲሉ፡ ይህን፡ ብርቱ የህልውናቸውን ጉዳይ፡ እንደገና እንዲያስቡበት፡ ኃያላኑን ለማንቃት ነው። በዛሬው የቅጣት ማዕበል ተጥለቅልቆ ሊዋጥ የሚንገላታውንም ኢትዮጵያዊ ትውልድ ለማትረፍ ነው። አዎን! የጥንት ፍጡራንን ከደመሰሰው የጥፋት ውኃ፡ ስምንት ሰዎችን እንዳተረፈችው፡ እንደኖኅ መርከብ፡ ይህች ጾም ተዘጋጅታ ቀርባለች።

ስለዚች ጾም ስንነጋገር፡ “'ጾም፥ ጸሎት፥ ምጽዋትና ንስሓ ምንድር ናቸው? ለምንስ ያስፈልጉናል?” ትሉኝ ይኾናል፤ ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ የሚኾነውን ቃል፡ ባጭር ልግለጽላችሁ! እንደምታውቁትና በእየራሳችሁ እንደሚሰማችሁ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ከራሱ ተፈጥሮና አካል ጀምሮ፡ እምነቱና ምግባሩ፥ አስተሳሰቡና አኗኗሩ፥ በጠቅላላ ህልውናውና ሕይወቱ፡ የእግዚአብሔር፥ በእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ነው። ይህንም፡ በሥነ ፍጥረትና በሥነ መለኮት ምሥጢራት ላይ ተመሥርቶና ታንጾ፥ ከእነዚህም ሠርፆና በእነዚህ ቆሞ፡ በሕያውነት የሚኖርበት ኹለንተናው ያረጋግጣል። እንዲህ ከኾነ፡ ኢትዮጵያዊዉን፡ ከዚህ መሠረታዊ አቋሙ ውጪ የሚያደርግ፥ ወይም፡ የተለየ የሚያስመስል፡ ድርጊትና አነጋገር ቀርቶ፡ ማሰቡ እንኳ እንዳይኖር ልንጠነቀቅ፡ በብርቱ ይገባናል።

ይህን ያልኩት፡ ያለ ምክንያት አይደለም፤ “ጾም” በሚለው ቃል ፈንታ፡ “የረኃብ ዓድማ” የሚለውን ባዕድ ይትበሃል ለመተካት፡ የሚካኼደውን ሙከራ፡ ከብዙዎች፥ ካልጠበቅኋቸው ወገኖች ጭምር፡ ተደጋግሞ በመስማቴ ነው፡፡ ይኹንና፡ ለኢትዮጵያዊ፡ “የረኃብ ዓድማ”፡ ምኑ ነው? ኢትዮጵያዊው፡ “ጾም”ን እንጂ፡ “የረኃብ ዓድማ”ን፡ የት ብሎ ያውቀዋል? ምኑም ስላይደለ፡ አያውቀውም፤ በ“ጾም” ፈንታ፡ “የረኃብ ዓድማ”ን ለመተካት የሚካኼደው ሙከራ፡ እንደሌላው፡ የባዕዳን ደባ ኹሉ፡ ኾነ ተብሎ፡ ኢትዮጵያዊዉን፡ ከእግዚአብሔር ለመለየት፡ ከተጻራሪው ጎራ ሥርፆ የተሠራጨ መርዝ መኾኑ፡ ግልጽ ነው፡፡

“ኢትዮጵያዊ ነኝ!” ባዩ ግን፡ ይኼን ሴራ፡ እንዴት ተቀብሎ ሊያስተጋባው እንደበቃ ያስገርማል! “ጾም” እኮ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለተዋሓደው፡ ለኢትዮጵያዊው ምግባር፡ መታወቂያ ምልክቱ ነው፡፡ “የረኃብ ዓድማ” ደግሞ፡ በእግዚአብሔር ለማያምኑ፡ ለአሕዛብና ለአረማውያን ወገኖች፡ መለያቸው እንዲኾን፡ ራሳቸው የመረጡት አገላለጽ ሊኾን ይችላል፡፡ “የረኃብ ዓድማ” የሰዎችና በሰዎች፥ ወደሰዎችም የሚያመራ ነው፤ ውጤቱም፡ በድንጋይ ላይ እንደፈሰሰ ውኃ፡ ተንኖ መቅረት፥ ማለትም፡ ፍጻሜው፡ ሞት ነው፡፡ “ጾም” ግን፡ የእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር፥ ወደእግዚአብሔርም ያደርሳል፤ ውጤቱም፡ በወንዝ ዳር እንደበቀለች ተክል፡ ለምልሞ፡ መልካሙን ማፍራት፥ ማለትም፡ ፍጻሜው ሕይወት ነው፡፡

ወገኖቼ! እስኪ፡ ቆም ብላችሁ፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በፊትና ከዚያ በኋላ፡ እስካኹን፡ የኾነውንና አኹን፡ እየደረሰብን ያለውን ኹሉ፡ በዓይነ ሕሊና ተመልከቱት! ለመኾኑ፡ ከዚህ ኹሉ ችግርና ውድቀት የደረስነው፡ ለምን ይመስላችኋል? ተራና ጥቃቅን መስለው ከሚታዩን፡ ከእኒህ ዓይነቶቹ ስሕተቶች፡ ባለመጠንቀቃችንና ነቅተን ባለመጠባበቃችን፥ ከዚህ የተነሣም፡ እያንዳንዳችን፡ የኃላፊነት ግዳጃችንን ባለመፈጸማችን አይደለምን? ነው እኮ! ታዲያ! ይህንኑ አውቀን፡ በዚህ ረገድ፡ ማስተዋልና ማመዛዘ ፥ የሚጠበቅብንንም ድርሻ፡ በያለንበት መፈጸም የምንጀምረው፡ መቼ ነው? የእስካኹኑና አኹን ያለንበት መከራ አይበቃንምን? ከቶ፡ ምን ነካን? ምንስ እስክንኾን ነው የምንጠብቀው? ኧረ ተዉ አይኾንም!?

“እንግዴህማ፡ እንንቃ እንጂ!” የሚለውን፡ የኢትዮጵያ ደወል፡ በዚህ አጋጣሚ እያሰማሁ፡ ወደጾም ርእስ እመለሳለሁ፡፡ “ጾም”፡ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ ራሱን ተቆጣጥሮ፡ ሥጋዊ ፍላጎቱን በመግታት፡ ወደልቦናው ተመልሶ፡ አፍአዊና ውሳጣዊ ኹለንተናውን ለመመርመርና ከክፉ አስተሳሰብ ለማጽዳት መቻል ነው፡፡ “ጸሎት”፡ ሰብአዊ ፍጡር፡ በሃይማኖት አምልኮና በእውነት መንፈስ ኾኖ፡ በመልኩ ከፈጠረው፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ ብቻ ለብቻ፥ በመሰሎች፡ ፍጹም አንድነትም፡ አብሮ መነጋገር ነው፡፡ “ምጽዋት”፡ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ ሌላውን፡ በባልንጀርነት ፍቅር አይቶና ተቀብሎ፡ ለዚያ ሰው፡ በአሳብ፥ በንግግርና በግብር፡ በጎ ነገርን ማድረግ ነው፡፡

በመጨረሻ፡ “ንስሓ”፡ ሕሊናችን የሚያውቀውንና የሚነግረንን፡ በአሳብ፥ በቃልና በድርጊት የፈጸምነውን ጥፋት፥ በደልና ክፋት፡ አምኖ፡ ራስን፥ ተበዳዩንና እግዚአብሔርን፡ ከልብ ይቅርታ መጠየቅ ነው፡፡ ራስንና እግዚአብሔርን ይቅርታ የመጠየቁ ግዳጅ፡ በመንፈስ ብቻ የሚፈጸም ስለኾነ፡ በዚህ ረገድ ችግር አይኖርም፤ የበደለንን ሰው፡ ይቅር ለማለት ኾነ፡ የበደልነውን ሰው፡ ይቅርታ ለመጠየቅ ግን፡ በአካል መገኘት ያስፈልገን ይኾናል፡፡ በዚህ በኩል ደግሞ፡ ይቅር የማለቱን ኾነ፡ ይቅርታ የመጠየቁን ግዳጅ፡ ከቻልን በግንባር፥ ካልቻልንም፡ በያለንበት ኾነን፡ በመንፈስና በእውነት መፈጸም ስለምንችል፡ በዚህ በኩል ላለው፡ በንስሓችን አፈጻጸምም ረገድ፡ ችግር እንደማይኖር፡ ልታውቁት ያስፈልጋል፡፡

እንዲህ አድርገን፡ እየራሳችንን፡ ከራሳችን፥ ከእግዚአብሔርና ከባልንጀራችን ጋር ስላስታረቅን፡ በውስጣችንና በውጫችን፡ ሰላምና ፍቅር ይሰፍናሉ፤ ሰውነታችንም፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት የበቃ ይኾናል፤ በዚህ ጊዜ ነው፡ እያንዳንዳችን፡ ቅዱስ ቁርባንን፡ በመቀበል፡ ጾማችንን፡ በእውነትና በትክክል መፈጸማችንን፡ ለራሳችን፥ ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራችን የምናረጋግጠው፡፡ የድኅነታችን (የመዳናችን) ማኅተም፡ የክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነውና፡፡ ያለዚያ፡ ድካማችን ኹሉ ከንቱ ይኾናል፡፡ ስለዚህ፡ ይህችን፡ የሦስት ቀን ጾመ ኢትዮጵያችንን፡ በትክክል ልንፈጽማት ይቻለን ዘንድ፡ ከአኹኗ አፍታ ጀምረን፡ ተገቢውን፡ የመንፈስ፥ የአእምሮና የአካል ትጥቅ ዝግጅታችንን ማከናወን ይገባናል፡፡

...፯

ሙሴ፡ በእግዚአብሔር አዛዥነትና አበጋዝነት፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ ከግብፅ የባርነት ቀንበር፡ ነጻ ካወጣቸው በኋላ፡ እየመራ፡ ለመጨረሻው ድል፡ በኤርትራ ባሕር ዳርቻ ቆመው በነበረበት ኹኔታቸው ዓይነት፡ ማለት ነው፡፡ ዛሬም፡ እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም መሪነት፡ ከዲያብሎስ ኃይላት አንጻር፡ በምናካኺደው፡ በዚህ፡ በ"ጾመ ኢትዮጵያ" የገድል ሰልፋችን ጊዜ፡ እየራሳችንን፡ ለመጨረሻው ድል ለማብቃት፡ እንዲህ፡ የተዘጋጀን ኾነን መገኘት ያስፈልገናል፡፡

እኒህ፡ ሦስት ቀናት፡ ከሠላሳ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ ያለማቋረጥ፡ እንደጎርፍ የፈሰሰውን፡ የኢትዮጵያን፡ የወንዶችና የሴቶች ልጆቿን፥ የሕጻናቷንና የወጣቶቿን፥ የጎልማሶቿንና የአዋቂዎቿን፥ የአዛውንቷንና የአረጋውያኗን ደምና እንባ፡ "በቃ!" ብሎ፡ የቃል ኪዳን አምላካችን እግዚአብሔር፡ ይቅርታውን እንዲለግሠን፡ የመጨረሻ ልመናችንን የምናቀርብባቸው ናቸው፡፡ አዎን! እኒሁ ሕዝቧ፡ በተከታታይ እየወረደባቸው ያለውን፡ ረኃብና ጥማት፥ እርዛትና እንግልት፥ ሕመምና ሥቃይ፥ ግፍና እሥራት፥ የመጠጊያ እጦትና ስደት፥ ግድያና የእርስ በርስ ዕልቂት፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ስለኃጢኣታችን ስርየት፡ ለአቤቱታና ለንስሓ እንደቀረበ መሥዋዕት አድርጎ እንዲቀበልልን የምንማጸንባቸው ናቸው፡፡

የፈጣሪያችንን ይቅርታና ምሕረት ለማግኘት ደግሞ፡ ከእርሱ ተለይተን፥ ቃል ኪዳኑንም አፍርሰን፡ የባዕዳኑንን ሥርዓት በመከተል ከቆየ በት፡ የስሕተት አካኼዳችን፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሰን፡ ሃይማኖታዊ አምልኳችንን፡ በቅድሚያ ልናስተካክል ያስፈልገናል፡፡ ይህችን የሦስት ቀናት ጾም፡ እንዲህ፡ እንደነነዌ ሕዝብ፡ እግዚአብሔር፡ በሚቀበለው መንፈስ ከፈጸምናት፡ ከሠላሳ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ ሳያባራ የቀጠለውን፡ የፈተና እሳትና የመከራ ማዕበል፡ ጨርሰን ማስወገድ እንደምንችል፡ መለኮታዊው የምሕረት ቃል ኪዳን አረጋግጦልናል፤ በምንም፡ የምንጠራጠረው አይደለም፡፡ ምናልባት፡ ይህን እውነታ፡ ለአንዳንዶች ማሳመን ካስፈለገ፡ በቅርቡ ተፈጽሞ የታየውንና ብዙዎቻችሁ፡ የምታስታውሱትን ተአምራዊ ድርጊት፡ እዚህ ላይ ማውሳቱ ይበቃ ይኾናል፤ ይኸውም፡ ከዛሬ አሥራ ስድስት ዓመታት በፊት፡ አገራችን፡ ገና፡ በደርግ የአገዛዝ ዘመን ሣለች፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ Voice of America በተባለው፡ በአሜሪካ ነፋስ ድምፅ አማካይነት፡ ተላልፎ ከነበረው ተመሳሳይ መልእክት በኋላ፡ ተከታትሎ፡ የደረሰው ድንቅ ነገር ነው፤ ያ፡ "ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስፈልገውና የሚጠቅመው፡ 'የነነዌን ጾም' በመሰለ፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ 'ጾመ ኢትዮጵያ'ን መጾም ነው!" የተባለለት ሃይማኖታዊ ምግባር፡ የደርግ አገዛዝ  መገርሰስ አሳየ፡፡

ይኹን እንጂ፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ፡ የፈተናው እሳትና የመከራው ማዕበል፡ በተለየ መልኩ፡ ለምን እየተራቀቀና እየተጠናከረ፥ እየተስፋፋም ቀጠለ? የእግዚአብሔርን ነገር፡ በየልቦናችን የሚያስገነዝበን ኢትዮጵያዊነታችን እኮ፡ የዚህን ምክንያት፡ ዘወትር፡ ለየራሳችን መንገሩን አላቋረጠም፤ ነገር ግን፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ይህ ኢትዮጵያዊነቱ፡ በየልቦናው የሚነግረውን ኹሉ፡ "እምቢ! አልሰማም!" አለ፤ የሚያዳምጠውና የሚከተለው፥ የሚፈራውም፡ ሰዎች፥ ያውም ባዕዳን የሚሉትንና ያስተማሩትን ብቻ ኾነ! ከዚህ የተነሣ፡ እየባሰ የኼደው፡ የፈተናው እሳትና የመከራው ማዕበል፡ በበለጠ እያጥለቀለቀውና እያሰጠመው ኼዶ፡ ይኸው፡ ዛሬ፡ ከመጨረሻው የጥፋት ፍጻሜ ደርሶ፡ ራሱን፡ አግኝቶታል፡፡

አዎን! ይህ ኹሉ መዓት፡ በትውልዱ ላይ የወረደበት፥ እየጸናበት የቀጠለውም፡ እግዚአብሔርንና ቃል ኪዳኑን፡ በክህደት፥ በዓመፅና በአመንዝራነት በመተዉ ነው፤ ይህን እውነታም፡ ይኸው ኢትዮጵያዊነቱ፡ እንደእስከዛሬው ኹሉ፡ ዛሬም፡ እነሆ እያስገነዘበው ይገኛል፡፡ ይኸው መከራ እንዲወገድለትም፡ በፈጣሪውና በቃል ኪዳኑ ላይ የፈጸመውን፡ ይህንኑ ኃጢኣቱን፡ በንስሓ በማጽዳት፡ ክህደቱን፡ በሃይማኖት፥ ዓመፁን፡ በአገልግሎት፥ አመንዝራነቱንም፡ በታማኝነት ተክቶና አድሶ፡ ከአምላኩ ጋር ዕርቅ እንዲያደርግ ይማፀነዋል፡፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ይህ መልእክት፡ ለኢትዮጵያውያን ኹሉ፡ እንዲደርስ በማሰብ የተላለፈበት፥ ተፈጻሚነትም ይኖረዋል ተብሎ የሚታመንበት፡ በቂ ምክንያት አለ፤ ይህም፡ ከሰላሣ ዓመታት በላይ የደረሰው፡ ሥፍር ቍጥር የሌለው መከራና ሥቃይ፡ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ልቦና፡ እንደነነዌ ሰዎች፡ ወደእውነተኛው የጸጸት መንፈስ ሊመልሰው እንደቻለ ስለተገመተ ነው፡፡ "ለንስሓ መብቃት" ማለት ይህ ነውና፡፡

የእግዚአብሔር ምሕረት እኮ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በተለይ፡ ከዛሬ ኹለት ሺህ ዓመታት ጀምሮ፡ እንደምንተነፍሰው ንጹሕ አየር፥ እንደምንመላለስበት የፀሓይ ብርሃን፥ እንደምንጠጣው ጥሩ ውኃና እንደቆምንባት ፍሬያማ ምድር፡ ይኸው፡ ከእያንዳንዳችንና ከኹላችን ጋር፡ ያለማቋረጥ፡ አብሮን ይኖራል፤ እውነተኛው ፍላጎት ካለንም፡ ይህን፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት፡ በቅጽበት ልናገኘው እኮ እንችላለን። ነገር ግን፡ ይህንኑ፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በየራሱ ውሳኔ፡ "የለም!" ብሎ፡ እንደሌለ ቆጠረው፤ "አልፈልገውም!" ብሎም፡ ከየራሱ አራቀው፤ ስለዚህ፡ አኹን፡ በዕድሜያችን፡ እነሆ፡ ከሰላሣ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ እየቀጠለ በኼደው፡ በዚህ፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት፥ ሥቃይና ጭንቀት ብቻ ሳይኾን፡ ደም መፋሰስ ጭምር በበዛበትና በጸናበት ህልውና ውስጥ እንዲኖር ተገድዶ፡ እነሆ፡ ሲዳክርና ሲባዝ ይገኛል።

የቃል ኪዳን አምላካችን እግዚአብሔር፡ የራስ ጸጉራችንን ሳይቀር ይጠብቃል፤ እንዲያውም፡ እኛን ሰዎችን፡ ከሰይጣን፥ ከኃጢኣትና ከሞት ለማዳን፡ ራሱን ቤዛ አድርጎ ሠውቶልናል፤ አንድ ፍጡሩ፡ መገደል ቀርቶ፡ ትንሽ ጉዳት እንኳ እንዲደርስበትም አይፈልግም። ለእኛ፡ ለቃል ኪዳን ተከታዮቹም፡ "ጠላቶቻችሁን ውደዱ! በክፉ ሥራቸው ፈንታ፡ በጎ አድርጉላቸው! የበደሏችሁንም ኹሉ ይቅር በሉ!" የሚል፡ የደግነት መመሪያን ሰጠን እንጂ፡ እንድንቀየማቸው፥ ከዚያም በኋላ፡ እንድንበቀላቸው እንኳ አልፈቀደልንም።

ሰዎች፡ በልዩ ልዩ መንገድ እንዲጎዱና እንዲሠቃዩ፥ እርስ በርሳቸውም ተጠላልተው እንዲጋደሉ ማድረግ የሚያስደስተው፥ ደማቸውንም አስፈስሶ፡ ያን መጠጣት የሚወድደው፡ ዲያብሎስ ነው፤ በተቃዋሚዎቻችንንም ላይ አድሮ፡ ይህንና ሌላውን ኹሉ፡ የክፋትና የጥፋት ድርጊት የሚያስፈጽመው፡ እርሱ መኾኑን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብዬ አልገምትም። በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ ቀድሞ፡ በኀቡዕ (በሥውር) ሲሠራ ከቆየ በኋላ፡ ከ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ጀምሮ ግን፡ ከነሠራዊቱ፡ በይፋ ነግሦ እንደሚገዛ፡ እነሆ፡ ለመላው ዓለም፡ ገሃድ በኾነው፡ የግፍና የጭካኔ ድርጊቱ፡ ተረጋግጦ ተመስክሩዋል፤ ይኸውም፡ ቍጥሩ፡ በእልፍ አእላፋት በሚታሰብ መጠን፡ ወንድማማችና እኅትማማች የኾኑት ኢትዮጵያውያን፡ በእርስ በርስና በድንበር ጦርነት፡ ደም በመፋሰስ የተላለቁበት፥ አኹንም እየቀጠለ እንዲኼድ የተደረገበት ታላቅ ደባ ነው። ለዚህም፡ ከሠላሳ ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ ባዕዳን ተጻራሪዎቻችን፡ በሚለግሡት ብቻ ሳይኾን፡ ከደኃው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተሰበሰበው የግብር ገንዘብ፡ ከእነርሱ እየተሸመተ ያለው፡ የጦር መሣሪያ ብዛት፡ በቂ ማስረጃ ይኾናል።

ታዲያ! በተንኰሉ፥ በገንዘቡና በጦር ኃይሉ ይዞታ ረገድ፡ እንዲህ ተሟልቶ የተደራጀውን፡ ይህን፡ የዲያብሎስንና የተጻራሪዎቻችንን የማጥቂያ ዝግጅት፡ ተቋቁሞ ለማስወገድ የሚቻለው፡ ሌላ ተወዳዳሪ ኃይል፡ ከእግዚአብሔር በቀር፡ ከቶ ማን ሊኖር ይችላል? አዎን! ማንም የለም፤ ስለዚህ ነው፡ ይህ "ጾመ ኢትዮጵያ" ያስፈለገው።

ወገኖቼ ሆይ! እግዚአብሔር፡ እንደሰው አይደለም። እንኳንስ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ምክንያት፡ ከእርሱ ጋር የቃል ኪዳን መተሣሠር ያለንን፡ እኛን፡ ኢትዮጵያውያንን ይቅርና፡ ሌላውን፡ ማንኛውንም፡ የተማመነበትንና በእውነት የሚጠራውን ፍጡሩንም እንኳ ቢኾን፡ አያሳፍርም፤ አሳፍሮም አያውቅም፤ እርሱ፡ እግዚአብሔር፡ በኪዳኑ፡ ፍጹም የታመነ ነው፤ በቃሉም፡ የጸና ነው፤ የቃል ኪዳን ተዋዋዩ የኾነ ፍጡሩ፡ ቃሉን አፍርሶ፡ ይክደዋል እንጂ፡ እርሱ፡ ፈጣሪ፡ በምንም መልክ፡ ከታማኝነቱ፡ አይነዋወጽም።

የሰዎች ቃል ኪዳንማ፡ ጉዱ፡ እንደገና ወጥቶና ተጋልጦ፡ ይኸው፡ ዕርቃኑን ታየ አይደለምን? የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የባዕዳን ሰዎችን፡ Capitalism, Socialism, Communism እና Democracy ከተባለው ፍልስፍናቸው ጋር፡ ፈልጓቸው፥ ፈቅዷቸውና አምኗቸው የተቀበላቸው መኾኑን፥ አብሮም፡ ሽር ጉድ ማለቱን መካድ፡ ከቶ ይቻላልን? አይቻልም፤ እያንዳንዱን ፍልስፍናስ፡ በተለያየ የአገዛዝ ፈሊጥ፡ በየተራ፡ በራሱና በአገሩ፥ በወገኑም ህልውና ላይ አስፍኖ፡ እንዲሠለጥን አላደረገምን? ስላደረገውማ፡ ይኸው፡ አኹን፡ ኹሉንም፡ በፍሬው፡ ራሱ፡ እያየው ነው! ያ ፍላጎቱ፥ ያ ፈቃዱና ያ እምነቱ ካስገኙለት መራራ ፍሬ፡ ባዕዳኑ፡ ጨምቀው የሞሉለትንም ጽዋ፡ ይኸው፡ ቋቅ እስኪለው ድረስ፡ ጨልጦ እንዲጠጣው እያስገደዱት ነው!

እንዲህ፡ ግራ የገባውና መቅኖ ያጣው፡ ይህ፡ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በዚህ ድርጊቱ፡ የተረፈው ነገር ቢኖር፡ አንድ ብቻ ኾኖ ይታያል፤ ይኸውም፡ ባለፉት ያልተቋረጡ ዘመናትና በአኹኑ ጊዜ፡ ይህንኑ፡ የባዕዳኑን ፈሊጥ ተከትሎ፡ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም፡ እየተሰለፈ፡ ወደእነዚሁ አጥቂዎቹ፡ ያለማቋረጥ የመጮህ ግዴታ ነው። ለዚያውም ቢኾን፡ ይህ ኹሉ፡ በከፍተኛ ድምፅ፡ በያለበት፡ የሚስተጋባው የኢትዮጵያውያን ጩኸት፡ ሰሚና ተቀባይ አላገኘም፤ እንዳላገኘም፡ ይኸው፡ በይፋ የታወቀ ኾኗል። ይህ፡ እውነት አይደለምን?

በኢትዮጵያዊነቴ፡ የቀረችኝን ግዳጅ በመፈጸም፡ በረዥም ሱባኤ ተግልዬ ከምገኝበት የተልእኮ ጽሙናዬ ኅትጕቶና አላሳርፍ ብሎ፡ ይህችን መልእክት እንዳደርስላችሁ፡ እኔንም ያነሣሣኝ፡ ይኸው፡ በኢትዮጵያና በዓለም አህጉራት ጎዳናዎችና አደባባዮች፡ በኃይል እየተስተጋባ ያለው፡ የኢትዮጵያውያን ጩኸት መኾኑን፡ ልደብቃችሁ አልሻም።

አዎን! ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ እንደታየው፥ ዛሬና ወደፊትም እንደሚታየው፡ የሚታመን፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሰው፡ ባዕዱም ኾነ፥ የራሴ የሚሉት ወገን ጭምር፡ ፈጽሞ ሊታመን አይቻልም። ይህን እውነታ፡ አረጋግጦ ለማስረዳት፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ከዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የበለጠና የተሻለ ምስክር ይኖራል ብዬ አላስብም። አባቶቻችንንና እናቶቻችንን፡ አልሰማናቸውም፥ ልንሰማቸውም አልፈለግንም እንጂ፡ እነርሱማ፡ "ሰውን፡ ውደደው እንጂ፡ አትመነው!" ደግሞም፡ "ሰውን ማመን፡ ቀብሮ ነው!" ሲሉ፡ አስቀድመው፡ አስጠንቅቀውን ነበር፥ እግዚአብሔርን ትቶ፡ በሰው የሚታመን ኹሉ፡ የተረገመ እንደኾነ እንደሚናገረው የመጽሐፍ ቃል፡ በሚቆጠረው ዘይቤያቸው።

ስለዚህ፡ እኛ ኢትዮጵያውያን፡ የግልም ኾነ፥ የጋራ ፍላጎታችን፡ በእርግጥ ይፈጸምልን ዘንድ፥ ጩኸታችንም፡ ተገቢውን ምላሽ ያስገኝልን ዘንድ፡ ምንጊዜም፡ ግንኙነታችንንና ንግግራችንን፥ ውለታችንንና ስምምነታችንን፡ ልናካኼድ፥ ልንፈጽምም የሚገባን፡ የቃል ኪዳን አምላካችን ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ነው፤ ይህንም፡ ከጥንት ከመሠረቱ፡ ከፈጣሪያችን የተቀበልነው ሥርዓታችን አበክሮ ያስገነዝበናል። ከዚህ የተነሣ፡ የምናምነው፡ እግዚአብሔርን፥ የምንታመነውም፡ በእግዚአብሔር ብቻ ሊኾን ይገባል፤ እርስ በርሳችን እንኳ፡ ልንተማመን የሚገባን፡ በእግዚአብሔር በኩል እንዲኾን ግድ ይኾናል፤ አለዚያ፡ አንዳችን፡ የአንዳችንን ውስጣዊ ማንነት ስለማናውቅ፡ በእየራሳችን መተማመን እንዴት ይቻለናል? አይቻለንም። በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት፥ በባልና ሚስት መካከል ያለው፡ የጋብቻ አንድነት ጭምር፡ በዚህ እውነታ ላይ የተመሠረተ ካልኾነ በቀር፡ ሊጸና አይችልም፤ እስከመፍረስ የሚደርሰውም፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን ማወቁ፡ ለማንም ሰው ይጠቅመዋል።

ኢትዮጵያዊዉን ሥርዓት፡ ለመግለጽ ያህል፡ ይህ አስተያየት ቢሠነዘርም፡ Capitalism, Socialism, Communism እና Democracy የሚባሉት፡ የባዕዳኑ ፍልስፍናዎች፡ "አይሠሩም፥ አይጠቅሙም" ማለት አይደለም፤ እነዚህ ፍልስፍናዎች፡ የሰዎች እንደመኾናቸው መጠን፡ ሰዎች፡ በፈለጉትና ለራሳቸው በሚጠቅሟቸው መንገድ፡ እንዲሠራባቸው የሚያደርጉበት፡ የተለያየ ሰውኛ ፈሊጥ አላቸው። ይህ ፈሊጥ፡ ሰውኛ ብቻ ሳይኾን፡ ሰይጣናዊ እስከመኾን ሊደርስ ስለሚችል፡ የእግዚአብሔር ከኾነው ሥርዓት ጋር ሊስማማ ቀርቶ፡ በሩቁ እንኳ ሊተያይ አይቻለውም። እስካኹን ደርሶ እንደታየው፡ ከሰብአዊነት ውጪ የኾኑ፡ የግፍ ድርጊቶች፡ በረቂቁም ኾነ፡ በግዙፉ መንገድ የሚካኼዱትና የሚፈጸሙት፡ በእነዚህ ፍልስፍናዎች ስም ኾኖ ይገኛል፤ ይህም፡ የፈሊጡ ምንጮች፡ የተፈለሰፉትና የተስተገበሩት፥ ሊሰፍኑም የ ሉት፡ "እግዚአብሔር የለም" የሚሉ አሕዛብ በሠለጠኑባቸው ኅብረተሰቦች መካከል በመኾኑ ነው፤ ስለዚህ፡ ውጤቱ፡ እንዲህ መኾኑ፡ ማንንም ሊያስደንቅ አይገባም።

እነዚህ ፍልስፍናዎች፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ፈጽመው ሊሠሩ እንዳልቻሉ፥ ወደፊትም፡ በኢትዮጵያዊው መሠረት ላይ ታንጸው ካልኾነ በቀር፡ ሊሠሩ እንደማይችሉ፡ ካለፉት ተከታታይ ተሞክሮዎችና አኹን እየበረታ ከቀጠለው አሳዛኝ ኹኔታ፡ ይኸው ተረጋገጠ። ይህም የኾነው፡ የእግዚአብሔሩን በሚከተለው፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓትና በእነዚህ የሰዎች ፍልስፍናዎች መካከል ባለው፡ መሠረታዊ የባሕርይ ልዩነት ምክንያት መኾኑን፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል፤ በተለይም፡ በባዕዳኑ ትምህርት የተራቀቁት ምሁራን፡ ይህን እውነታ፡ ራሳቸው ተገንዝበውት፡ እየራሳቸውንና እነርሱ፡ "መሃይም" የሚሉትን፡ ወገናቸውን፡ ከዚህ ገዳይ ስሕተት ሊያድኑ ይገባቸዋል።

በእነዚህ የሰዎች ፍልስፍናዎች ውስጥ፡ ተጋንነው የሚወሱት፡ የግል ነጻነትን፥ የመብት መከበርንና የራስ አስተዳደርን የመሰሉት ዓላማዎች እኮ፡ ዛሬ፡ በምድር ላይ ካሉት የዓለም መንግሥታት ኹሉ፡ ቀዳሚ በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት ዘንድ፡ ከፈጣሪ የታዘዙ መመሪያዎችና ዐበይት ተግባራት ኾነው፡ እየተሠራባቸው፥ እስከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ድረስ፡ "ማኅበር" በሚለው አቋም፥ በተለይም፡ በአኵስም ጽዮን አስተዳደር፡ ለናሙና፡ በሕያው ቅርስነት፡ በይፋ ሲካኼዱ ኖረዋል፡፡ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ ይህን የራሱን ሥርዓት፡ ከቁም ነገር ስላልቆጠረው፡ ንቆ እስከተወው፥ በትክክለኛው መንገድ እንዳይሠራበትም፡ ኾነ ብሎ እስካገለለው ድረስ ማለት ነው፡፡

እንግዴህ ወዲህማ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ኹሉንም ዓይነት የሰዎች ፍልስፍና፡ ከነፈሊጦቹ ስላየው፥ በሙከራና በመከራም ስላለፈበት፡ ብዙ ጉድለትና ሓሰት ከተገኘበት፡ ከሰዎች የአገዛዝ ፍልስፍናና ፈሊጥ ይልቅ፡ በእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት እየተመሩና እየተዳደሩ መኖር፡ የተሻለና የበለጠ፡ መልካም ሕይወትን እንደሚያተርፍ፡ ራሱ አምኖ፡ ሌላውን እንደሚያሳምን አልጠራጠርም፤ ይህም፡ እውን የሚኾነው፡ እንኳንስ ለኢትዮጵያውያን፡ ለሌሎቹ የዓለም ሕዝቦችም ቢኾን፡ ሰዎች፡ እግዚአብሔርንና የእርሱ የኾነውን ኹሉ፡ በእውነት ከፈለጉ፥ በእውነትም ከሠሩበት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

በዚህ አጭር ሓተታ እንደተብራራው፡ በጾመ ኢትዮጵያ አማካይነት፡ በተጸጸተ ልቦና፡ ወደእግዚአብሔር የሚቀርበው፡ የኢትዮጵያውያን ጩኸት፡ አቀራረቡም፥ የሚያስከትለውም ውጤት፡ ከዚያ፡ ከሰውኛው የተለየ እንደሚኾን ግልጽ ነው፡፡ አዎን! ኢትዮጵያዊው አቤቱታ፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ ለእግዚአብሔር፡ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብ ስለኾነ፡ በጽሙናና በጸጥታ የሚፈጸም እንጂ፡ በጩኸትና በመፈክር፥ በሰልፍና በግርግር የሚካኼድ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ "የእናት ምልጃ፡ ፊት አያስመልስ፤ አንገት አያስቀልስ!" እንዲሉ፡ እናት ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡ እጆቿን፡ ወደልጇ ዘርግታ ፍላጎቷን፥ ጥያቄዋን፥ ምስጋናዋን የምትገልጽበት ሃይማኖታዊ ምግባር ነው፤ ውጤቱ፡ በእምነት የሚጠበቅ፥ በሰዓታት ወይም በቀናት ሳይኾን፡ በቅጽበታት ውስጥ አስደሳች መልስን የሚያሰጥ ኾኖ፡ ኹሉን አቀፍ የኾነ፡ መልካም ፍሬን እንደሚያስገኝም አይጠረጠርም፡፡

እማታውቁ ካላችሁ፡ እንዳሳውቃችሁ፥ "አውቀናል" ብላችሁ፡ ነገር ግን፡ ለማመን ላልፈቀዳችሁ ደግሞ፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ አሳምናችሁ ዘንድ እንድትፈቅዱልኝ የምጠይቃችሁ፡ አንድ ቊም ነገር አለኝ፤ እርሱም፡ "እውነተኛ" ኢትዮጵያዊን፡ በየዘመናቱ፡ ከሌላው ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ የተለየ አድርገውት፡ በዓለሙ ኅብረተሰብ ዘንድ፡ የዛሬውን የመሰለ ችግርን ከፈጠሩበት ባሕርያቱ መካከል፡ ቀዳሚ ኾኖ የሚጠቀሰውን ይመለከታል፤ ያም፡ ከማይገሠሠው ነጻነቱ ጋር፡ ከፈጣሪው በቀር፡ ሌላ ፍጡርን፥ ሌላ እውቀትን፥ ሌላ ሀብትን እና/ወይም፡ ሌላ ኃይልን፥ በገዢነት ለመቀበል፡ ፈቃደኛ አለመኾኑ ነው፡፡

ለኢትዮጵያዊው፡ በሥጋውም፥ በነፍሱም፡ ፈጣሪውና አምላኩ ብቻ ሳይኾን፡ አባቱና ሕይወቱ፥ ንጉሡና ካህኑም፡ *"ምአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* በተባለው፡ በመራሔ መንግሥቱ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት የተገለጠው እግዚአብሔር ነው፤ እንዲሁም፡ እናቱና ሃይማኖቱ፥ አገሩና ንግሥቱም፡ *"ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!"* የተባለችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ ማንም ፍጡር፡ ቢወድም፡ ቢጠላም፥ ቢቀበለውም፡ ቢቃወመውም፡ ኢትዮጵያ፡ ጥንትም፥ ዛሬም፥ ለዘለዓለምም፡ ከነሕዝቧ፥ ከነመንግሥቷና ከነምድሩዋ፡ የእግዚአብሔር መኾኗን ማመን ግድ ይኾንበታል፡፡

ደግሞም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በአገር ውስጥም ኾነ በውጭ አገር፡ በእርሻ፥ በንግድ፥ በተግባረ እድ፥ በዘብና በውትድርና፥ በትምህርት፥ በጽሕፈት፥ በምሕንድስና፥ በኪነት፥ በሥነ ጥበብ፥ በድርሰት፥ በሕክምና፥ በዳኝነት፥ በአስተዳደር፥ በክህነትና በአማካሪነት፥ በሌሎችም ሙያዎች ላይ ተሠማርቶ፡ በገጠር፥ በሜዳ፥ በዱር በገደል፥ በብቸኝነት፥ በማይምንነት፥ በረኃብ፥ በጥማት፥ በእርዛት፥ በደዌ ሥቃይ፥ በእሥራት፥ በስደት፥ በኀዘንና በድህነት የሚታገለው፡ ብቻ ሳይኾን፡ በከተማ፥ በመንደር፥ በቤት፥ በትዳር፥ በሥራ፥ በነጻነት፥ በጥጋብ፥ በምቾት፥ በጤንነት፥ በደስታ፥ በምሁርነትና በሥልጣን የተደላደለው ጭምር፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ካለ፡ ራሱን፡ ለዚህ፡ ለኢትዮጵያዊው፡ የእግዚአብሔር ልጅነት፥ ለመንግሥቱም ዜጋነት፥ ወራሽነትና አገልጋይነት፡ ማብቃት ይኖርበታል፡፡

ታዲያ፡ “ዘለዓለማዊ ነጻነትን ካጎናጸፈኝ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመልኩ በመፈጠሬ፥ ከመንፈሱም በመወለዴ፡ ፍጡሩና ልጁ፥ የመንግሥቱም ዜጋ፥ አገልጋይና ወራሽ ኾኜ፡ በእርሱ ፈጣሪነትና አምላክነት፥ አባትነትና ንጉሥነት፥ በቅድስት እናቱም፡ በድንግል ማርያም፡ እናትነትና ሃይማኖትነት፥ አገርነትና ንግሥትነት ከመኖር በቀር፡ ለሌላ ባዕድ አልገዛም!” አስብሎ የሚያስጨክን፥ ይህን፡ የማይናወጽና የማይበገር ባሕርይን፡ ይኼ ኢትዮጵያዊ፡ ከቶ፡ ከየት አገኘው? ከፈጣሪውና ከወላጆቹ፡ በተፈጥሮና በቃል ኪዳን ስለተቀበለውና ስለወረሰው አይደለምን? አዎን! እውነታው፡ ይህ ነው፡፡

እያንዳንዳችን፡ ኢትዮጵያዊነትን፡ እንዲህ፡ በነፍስ ወከፍ የተቀበልነውና የወረስነው፡-

፩ኛ፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔርና ከወላጆቻችን ከኾነ፥

፪ኛ፡ ለየራሳችን፡ በየግላችን፡ እንኖረውና እንጠቀምበት ዘንድ፥ እንገለገልበትና እናገለግልበትም ዘንድ፡ ከኾነ፥

፫ኛ፡ አኹንና ወደፊት፡ ሠርተንበት፥ የአገልግሎትና የ ስሓ ፍሬንም አፍርተንበት የተገኘን ስለመኾኑ፡ እያንዳንዳችን፡ በየሕሊናችን፥ በወገኖቻችንና በእግዚአብሔር ዘንድ፡ በነፍስ ወከፍ የምንጠየቅበት ከኾነ፡ ይህ፡ “ጾመ ኢትዮጵያ”፡ ለኹሉ የሚበጀውን ጣፋጭ ፍሬ ሊያበረክት ይበቃ ዘንድ፡ በትክክለኛው የእውነት መንፈስ እንዲፈጸም የማድረጉ ኃላፊነት፡ የየራሳችን መኾኑን ማወቅና ማረጋገጥ አለብን፡፡

እንዲህ ከኾነ፡ ይህን ጾም፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ኾነን፡ ልንጾመው ይገባናል፡፡ የኃጢአታቸው ጽዋ ሞልቶ፡ ሊጠፉ በቀረቡት፡ የሰዶምና የገሞራ ከተሞች ውስጥ፡ አሥር ጻድቃን ቢገኙ፡ ከተሞቹ እንደማይጠፉ፡ እግዚአብሔር፡ ለወዳጁ፡ ለአብርሃም አረጋግጦለት እንደነበረ ይታወሳል፤ አኹንም፡ ፈጣሪ፡ በዚህ ጾም ምክንያት፡ ምናልባት፡ እያንዳንዳችንን፡ “ከአሥሩ ጻድቃን መካከል፡ እንደአንዱ ቆጥሮ፡ የቃል ኪዳን አገሩን፡ ኢትዮጵያንና የቃል ኪዳን ሕዝቡን ኢትዮጵያውያንን ይታደጋቸው፥ ከመጥፋትም ያድናቸው ይኾናል!” ብለን በማመን ብንጾመው፡ ይሠራልናል፡፡ (ዘፍጥ. ፲፰፥ ፳፪-፴፪፡፡)

እንግዴህ፡ የሦስቱ ቀኖች “ጾመ ኢትዮጵያችን”፡ በሃይማኖት ተስፋ የምንጠብቀውን፡ ይህን የመሰለውን፡ መልካም ፍሬ እንዲያስገኝልን፡ ምን ማድረግ አለብን? ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱን፡ እያንዳንዳችን እንድንሰጥ ይጠበቅብናል፤ ይኸውም፡ “እየራሳችንን፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት ለይተን ካጠፋንበት አኗኗራችንና ለሞት ከዳረግንበት አስተሳሰባችን፡ አስቀድመን፡ በእውነተኛ ንስሓ መልሰን ልናዘጋጀው ይገባናል!” የሚለው ነው፤ እንደነነዌ ሰዎች፥ ወይም፡ ከሕመሙ ለመዳን፡ በግድ፡ መራራ መድኃኒትን መውሰድና ከባድ ሕክምናን መቀበል እንዳለበት ጽኑ በሽተኛ ማለት ነው፡፡ አዎን! መሥዋዕትነትን፡ እንዲህ ለመክፈል፡ በቆራጥነት መዘጋጀትማ፡ ለእያንዳንዳችን፡ አይቀሬ ግዳጅ መኾኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ግብ ለመድረስ፡ ይቻለን ዘንድ፡ የሚከተለውን፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እጠቅስላችኋለሁ፡-

ይህም ቃል፡ ገናናው፡ ኢትዮጵያዊው መሪያችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱን፡ እንደይቅር ባዩ ርኅሩኅ አባት፥ እኛን እያንዳንዳችንን ደግሞ፡ እንደአጥፊው ልጁ አስመስሎ፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ዓመት፡ በምሳሌ የነገረን ነው፤ ስለዚህ፡ እየራሳችሁን፡ በዚያ፡ በታናሽ ልጁ ቦታ በማስቀመጥ፡ መልእክቱን ለየግላችሁ እንድትጠቀሙበት አሳስባችኋለሁ!

> “አንድ ሰው፡ ኹለት ልጆች ነበሩት፤ ከእነርሱም፡ ታናሹ፡ አባቱን፡ 'አባቴ ሆይ! ከገንዘብህ፡ የሚደርሰኝን፡ ከፍለህ ስጠኝ!' አለው፡፡
>
> “አባቱም፡ ከፍሎ ሰጠው፡፡
>
> “ከጥቂት ቀን በኋላም፡ ያ፡ ትንሹ ልጁ፡ ገንዘቡን ኹሉ ሰብስቦ፡ ወደሩቅ አገር ኼደ፡፡ በዚያም፡ በመዳራት (በመሸታ ቤት በመደሰት)፡ ገንዘቡን ኹሉ አባክኖ፡ ጨረሰ!
>
> “ገንዘቡን ኹሉ አባክኖ በጨረሰበት ጊዜም፡ በዚያ አገር፡ ጽኑ ረኃብ መጣ! እርሱም፡ ፈጽሞ ደኸየ፡፡ ኼዶም፡ ከዚያ አገር ሰዎች፡ ለአንዱ ተቀጠረ፡፡

“ቀጣሪውም፡ አሳማዎችን ይጠብቅ ዘንድ፡ ወደእርሻው ቦታ ሰደደው፡፡ እዚያም፡ አሳማዎቹ በልተው ከሚተርፋቸው አሠር ለመመገብ እስከመፈለግ ድረስ ተራበ፤ ነገር ግን፡ ያንንም እንኳ፡ የሚሰጠው አላገኘም፡፡

“በዚህ ጊዜ፡ ወደልቡ ተመልሶ፡ እንዲህ ሲል አሰበ፡- "በአባቴ ቤት፡ እህል የሚተርፋቸው፡ አገልጋዮችና ደሞዝተኞች ስንቶች ናቸው? እኔ ግን፡ እዚህ፡ በረኃብ ልሞት ነው፡፡ ስለዚህ፡ አኹኑኑ ተነሥቼ፡ ወደአባቴ እኼዳለሁ፤ እንዲህም እለዋለሁ፡- 'አባቴ ሆይ! እኔ፡ በሰማይም፥ በፊትህም በድያለሁ፤ እንግዲህ ወዲህም፡ ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከአገልጋዮችህ፡ እንደአንዱ አድርገኝ!'" ተነሥቶም፡ ወደአባቱ ኼደ፡፡

“አባቱም፡ ገና ከሩቅ ሲያየው፡ ራራለት፤ ሮጦ፥ አንገቱንም አቅፎ ሳመው፡፡

“ልጁም፡ "አባቴ ሆይ! በሰማይም፥ በፊትህም በደልሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህም፡ ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ብቻ፡ ከአገልጋዮችህ፡ እንደአንዱ አድርገኝ፡፡" አለው፡፡

“አባቱም፡ አገልጋዮቹን፡ እንዲህ አላቸው፡- "ከኹሉ የተሻሉትን ልብሶች፡ ቶሎ አምጡና፡ አልብሱት! ለጣቱ፡ ቀለበት፥ ለእግሩም ጫማ አድርጉለት! የሰባ ፍሪዳም አውጡና እረዱ! እንብላ! ደስም ይበለን! ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፥ ተነሥቷልና፤ ጠፍቶም ነበር፥ ተገኝቷልና፡፡" ደስም ይላቸው ነበር፡፡ (ሉቃ. ፲፭፥ ፲፩-፴፪፡፡)

እኛም፡ በዚህ ጾመ ኢትዮጵያችን አማካይነት፡ እንደዚህ ልጅ፡ ከክህደትና ከዓመፅ፥ ከአመንዝራነትም ኃጢአታችን፡ ከልብ ተጸጽተን፡ በእውነት ልንመለስ ይገባናል፤ ይህን ካደረግን፡ የፈጣሪያችንን ይቅርታና ምሕረት፡ ያለጥርጥር እንደምናገኝ፡ ይህ መለኮታዊ ቃል ያረጋግጥልናል፡፡ የኢትዮጵያዊነታችን መገለጫና መታወቂያ ከኾኑት፡ ከሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መካከል፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የተቀዳጀነው፥ እኛም፡ በቅዱስ ቍርባን፡ ዘወትር የምናጸናው የቃል ኪዳን ማኅተም፡ ኪዳነ ምሕረት ነው፡፡ ይህንም፡ በየዓመቱ፡ በየካቲት ፲፮ ቀን፡ በታላቅ የኢትዮጵያዊነት ስሜት በምናከብራት፡ የኪዳነ ምሕረት በዓላችን፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በአዋጅ ስናሳውቅ ኖረናል፡፡ ይህች፡ ዓመታዊዋ የኪዳነ ምሕረት በዓላችን ቀን፡ በምሕረት ቃል ኪዳኗ መሠረት፡ ለዘንድሮዋ “ጾመ ኢትዮጵያ” የምታበረክትልንን፡ ልዩ የ ስሓ ፍሬ ለመሰብሰብ፡ እነሆ፡ በሃይማኖት ተስፋ እንጠብቃለን፡፡

በመጨረሻ፡ የ“ጾመ ኢትዮጵያ” ምሕላችንን፡ ቸሩ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናታችን ድንግል ማርያም፡ ይቀበሉልን ዘንድ፥ ለምንጠብቀው መልካም የድል ፍሬም ልናበቃው ይቻለን ዘንድ፡ እያንዳንዳችን፡ በእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት የአምልኮ መንፈስ ኾነን፡ ልናቀርበው፥ ቅዱስ ቍርባንንም በመቀበል ልንፈጽመው እንደሚገባን፡ እስካኹን ከተሰጠው ማብራሪያ፡ በሚበቃ የተገነዘባችሁት ይመስለኛል፡፡ እንዲህ ከኾነ፡ የኢትዮጵያዊነታችንን ምንነት፡ አስቀድመን፡ ለየራሳችን፡ በትክክልና በግልጽ ማወቅ፥ ቀጥለን፡ ለእግዚአብሔርና ለሌላው ሰብአዊ ፍጡር፡ ማሳወቅ አለብን፤ ይልቁንም፡ ያለንበት ዘመን፡ እጅግ አሳሳችና አደናጋሪ በመኾኑ፡ የዚህኑ፡ የኢትዮጵያዊነታችንን፡ እውነተኛነቱን ብቻ ሳይኾን፡ ከማናቸውም ዓይነት ሰብአዊ ስሕተትና ሰይጣናዊ ሓሰት ሳይቀር፡ የጠዳና የጠራ፡ ፍጹም መለኮታዊና ንጹሕ ኢትዮጵያዊ መኾኑንም፡ ማረጋገጥ ግድ ይኾንብናል፡፡ ይህን የመሰለውን ጥንቃቄ እናደርግ ዘንድ፡ ያለፍንበትና የምንገኝበት መከራ፡ አስተምሮናል፡፡

ስለዚህ፡ በዚህ ረገድ ያለውን ፍላጎታችንን ሊያሟሉልን የሚችሉ፡ አራት የኢትዮጵያውያንን መመሪያ ክታቦች፡ ግእዙን ብቻ ሳይኾን፥ ኢትዮጵያኛውንና እንግሊዝኛውን ቅጂዎች ጭምር፡ ከዚህ መልእክት ጋር አያይዤላችኋለሁ፤ እነዚህ ጽሑፎች፡ የኢትዮጵያዊነትን መሥፈርቶች ያካተቱና በጸሎት መልክ የተዘጋጁ፥ እግዚአብሔር፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ላይ የጻፋቸውንና በየልቦናው ውስጥ ያሳደራቸውን ቅዱሳት ኪዳናት የያዙ ናቸውና፡ በማስተዋልና በማተኰር ተጠቀሙባቸው፡፡

ደግሞም፡ በዚህ መልእክት ውስጥ ስለተጠቀሱት ቁም ነገሮች፡ በበለጠ ለማወቅና በዝርዝር ለመረዳት፡ ከዚህ የሚከተሉትን መጻሕፍት፡ በኢትዮጵያና በውጭ አህጉራት አብያተ መጻሕፍትና መደብሮች፥ ወይም፡ ከላይ በመጀመሪያው ገጽ ግርጌ በተጻፉት፡ በአገልግሎታችን አድራሻዎች በኩል፡ ልታገኟቸውና ልትመለከቷቸው ይቻላል። እነዚህም፡- "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፉረጃ!" Ethiopia: The Classic Case እና "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት"፡- "አንደኛ መጽሐፍ"፥ "ኹለተኛ መጽሐፍ" እና "ሦስተኛ መጽሐፍ" የተባሉት ናቸው።

እነዚህ መጻሕፍት፡ ለበርካታዎቹ የዘመኑ ጥያቄዎች፡ የሰውኛውን የ"እውነት" አቀራረብ ፈሊጥ በመከተል ሳይኾን፡ የእግዚአብሔር በኾነችው፡ መለኮታዊት እውነት ላይ በተመሠረተ ቀጥተኛነትና ግልጽነት፡ ትክክለኞች መልሶችን የሚሰጡ ናቸው። ከጥያቄዎቹም መካከል፡ "ኢትዮጵያ ማናት? ኢትዮጵያዊው ማነው? ኢትዮጵያዊነትስ ምንድር ነው? እኔ ማነኝ? እግዚአብሔር ማነው? ባልንጀራዬስ? የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ኹኔታ፡ እስከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ድረስ፡ እንዴት ነበር? ከዚያ በኋላና እስካኹን ያለውስ እንዴት ነው? በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የደረሰውን ታላቅ ውድቀት ያመጣው ጠንቅ፡ በእርግጥ ምንድር ነው? ከኹሉም በላይ፡ ለዛሬውና ለወደፊቱ፥ ለጠቅላላውም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ችግር፡ ፍጹሙና ዘለዓለማዊው መፍትሔ፡ ከቶ ምንድር ነው?" የሚሉት ይገኛሉ።

ይህ መልእክት፡ በማናቸውም ዓይነት መስመርና መልኩ የሚደርሳችሁ ኹሉ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ፡ ራሳችሁ ተቀብላችሁ፡ እንድትፈጽሙት ብቻ ሳይኾን፡ ዓቅማችሁ በፈቀደ መጠን፡ ለሌሎችም እንድታስተላልፉት ያስፈልጋችኋል። ለዚህም፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም፡ ኃላፊነትና አደራ፥ ተጠያቂነትም እንዳለባችሁ፡ ልታውቁት ይገባል፤ ይህን ኃላፊነት፥ አደራና ተጠያቂነት የተቀበላችሁትም፡ ከሰው ሳይኾን፡ ከባለመክሊቶቹ፡ አምላካችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስና እናታችን ድንግል ማርያም ስለኾነ፡ በፊታቸው በምትቀርቡበት ጊዜ፡ ከፍሬው፥ ወይም፡ ከትርፉ ጋር እንድታስረክቧቸው የሚጠይቋችሁ፡ እነርሱ መኾናቸውን፡ የተገነዘባችሁት ይመስለኛል።

የ"ጾመ ኢትዮጵያ" ማሳሰቢያ የኾነው፡ ይህ መልእክት ደርሷችሁ፡ ጾሙን፡ ለመፈጸም ፈቃደኞች ከኾናችሁ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ፩ኛ፡ የመንፈስ ቅዱስ ወገን መኾናችሁን፡ በይፋ መመስከራችሁ ነው፤ ይህም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ምልክት እያማተባችሁ፡ "በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፥ በቅድስት ሥላሴ፡ እንዘ አአምን፥ ወእትመነፀን፤ እክሕደከ ሰይጣን! በቅድመ ዛቲ፡ እምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ እንተ ይእቲ፡ ስምዕየ ማርያም ጽዮን፤ ለዓለም ዓለም።" ማለትም፡ "ልዩ በኾነች ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡ በአብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜና ተማጽኜ፡ እናቴና መጠጊያዬ፥ ምስክሬና ቤተ ክርስቲያኔ በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ፊት፡ አንተን ሰይጣንን ክጄሃለሁ! ለዘለዓለሙ።" ብላችሁ በምትጀምሩት ጸሎታችሁ ይታወቃል፤ ፪ኛ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታችሁን፡ በገሃድ ማረጋገጣችሁ ነው፤ ይኸውም፡ በዚህ ድርጊታችሁ፡ ፈጣሪያችሁን ከነእናቱ፡ ማስደሰታችሁ፥ የየግላችሁን ኢትዮጵያዊ ግዳጅም፡ መወጣታችሁ ነውና፡ በጾሙ ማብቂያ ጊዜ፡ ረክታችሁ፡ እየራሳችሁን ደስ ብሏችሁ ታገኙታላችሁ።

አቋማችሁ ይህ ከኾነ፡ በግል፥ በቤተሰብ እና/ወይም፡ በማኅበር ለማካኼድ የምትሹትን የጾማችሁን ሥርዓት፡ በተሟላ ይዘትና ቁመት ለማከናወን፡ ምቹና ቀና ይኾንላችሁ ዘንድ፡ በጸሎትና በስግደት፥ በመዝሙርና በምንባብ ዝግጅታችሁ በኩል፡ የሚረዳችሁን ዝርዝርና ቅደም ተከተሉን የሚያሳየውን ጽሑፍ መመሪያ፡ ከዚህ ጋር፡ በመጨረሻዎቹ ገጾች ላይ፡ በተጨማሪ፡ አባሪ አድርጌ፡ ልኬላችኋለሁ። የጸሎቶቹንና የመዝሙራቱን ዜማ ለመስማትና ለማወቅ ከፈለጋችሁ፡ የተቀረፀውን የዜማውን ድምፅ የያዘውን ሸክላ፡ በአገልግሎታችን አድራሻ ልትጠይቁ ትችላላችሁ።

መሓሪው ፈጣሪያችን፡ የ"ጾመ ኢትዮጵያ" ምግባራችንን በሰላም አስፈጽሞ፡ የቃል ኪዳናችን ፍሬ የኾነውን፡ ምሕረቱን ለምናከብርባት፡ ለየካቲቷ ፲፮ ቀን በዓላችን ያብቃን!

\+ \+ \+ \+ \+ \+ \+

# የ"ጾመ ኢትዮጵያ" ሥርዓተ ጸሎት።

ጸሎቱ፡ በግል÷ በቤተሰብ÷ ወይም፡ በማኅበር÷ በሠርክ (ወደማታ ጊዜ)÷ አለዚያ፡ በማናቸውም ጊዜ÷ በግእዝ÷ ወይም፡ በኢትዮጵያኛ÷ የዜማው፡ በዜማ÷ አለዚያ፡ በንባብ ብቻ ሊባል÷ ምንባቡም፡ በተካፋዮቹ ተሳትፎ ሊካኼድ ይቻላል።

፩ኛ፡ የመክፈቻ ጸሎት፤ ካህን ካለ፡ በካህኑ÷ ካህን ከሌለ፡ በዲያቆኑ÷ ዲያቆንም ከሌለ፡ ከምእመናን መካከል፡ በአረጋዊው÷ በቀዳሚው÷ ወይም፡ በአንዱ፡ ይመራል። ተካፋዮቹ፡-

- "አአትብ ገጽየ" እያሉ፡ አራት ጊዜ በመስገድ ጸሎታቸውን ይጀምሩ። ስግደቱ፡ ፩ዱ፡ ለእግዚአብሔር ለ፩ነቱ÷ ፫ቱ፡ ለ፫ነቱ ነው።
- የኢትዮጵያውያንን የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች፡ በኅብረት ይበሉ።
- "ሰላም ለኪ!"ን፡ አንድ ጊዜ ሰግደው፡ ከ"ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም" ጋር ከጸለዩ በኋላ፡ አያይዘው፡ የዕለቱን "ውዳሴ ማርያም" በተራ እየተቀባበሉ በመድገም፡ በ"አቡነ ዘበሰማያት" እና በ"በሰላመ ገብርኤል" ያጠቃልሉ።
- ኹሉም፡ ከምድር ላይ፡ በግንባራቸው ተደፍተው፡ የነቢዩ ዳንኤል፡ ሦስት ጓደኞች፡ አናንያ÷ አዛርያ÷ ሚሳኤል፡ በስደት አገር፡ በባቢሎን የእሳት ነበልባል መካከል ሣሉ፡ መለኮታዊዉን ምሕረት በመጠየቅ፡ የጸለዩትን፡ የ ስሓ ጸሎት ይበሉ።
- "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!" የሚለውን፡ የመዝ. ፷፯÷ ፴፩-፴፪ ጥቅስ፡ በምስባካዊው ሥርዓት፡ ሦስት ጊዜ ያዚሙት።

፪ኛ፡ ምንባብ፤ ለሦስቱ ዕለታት ከተመደቡት ምንባቦች መካከል፡ የመጀመሪያው ዕለት፡ በተራ ፊደል (ሀ.) ያለው ጥቅስ፡ ከላይ፡ በ፩ኛው ተራ ቁጥር በተመለከተው መሠረት፡ ይነበብ።

የመጀመሪያው (የሰኞ) ዕለት፡-

ሀ. ዮና. ምዕ. ፩ እና ፪፤
ለ. ፩ኛ ነገ. ምዕ. ፲÷ ቍ. ፩-፲ እና ፲፫፤
ሐ. ሮሜ፡ ምዕ. ፰÷ ቍ. ፳፰-፴፱፤
መ. መዝ. ፷፯፤
ሠ. ማቴ. ምዕ. ፲፰÷ ቍ. ፲፱-፴፭።

የኹለተኛ (የማግሰኞ) ዕለት፡-

ሀ. ዮና. ምዕ. ፫፤
ለ. ኤር. ምዕ. ፴፰÷ ቍ. ፩-፲፫፤
ሐ. ዕብ. ምዕ. ፲፪÷ ቍ. ፩-፲፬፤
መ. መዝ. ፸፩÷ ቍ. ፳፰-፴፱፤
ሠ. ሉቃ. ፲፭÷ ቍ. ፩-፴፪።

የሦስተኛው (የረቡዕ) ዕለት፡-

ሀ. ዮና. ምዕ ፬፤
ለ. አሞ. ምዕ. ፱÷ ቍ. ፩-፲፪፤
ሐ. ፩ኛጴጥ. ምዕ. ፬÷ ቍ. ፯-፲፱፤
መ. መዝ. ፸፫፤
ሠ. ማር. ፲፫።

፫ኛ፡ "ሕዝባዊው እግዚኦታ" የሚባለውን ምሕላ፡ በኹለት ወገን ኾነው፡- እንደቦታው ምቹነትና እንደሰዓቱ መጠን፡ ፫፡ ፫ ጊዜ÷ ወይም፡ ፯፡ ፯ ጊዜ÷ ወይም፡ ፲፪፡ ፲፪ ጊዜ፡ በሕዝባዊ ዜማ ይበሉትና ሲጨርሱ፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ተደፍተው ይስገዱ።

ቀጥሎ፡ ምንባብ፤ ለሦስቱ ዕለታት ከተመደቡት ምንባቦች መካከል፡ የዕለቱ፡ ከላይ፡ በ፪ኛው ተራ ቁጥር÷ በተራ ፊደል (ለ.) ያለው ጥቅስ፡ በ፩ኛው ተራ ቁጥር በተመለከተው መሠረት፡ ይነበብ።

፬ኛ፡ "ሃሌ ሉያ!" በሚለው መክፈቻ፡ ከምሕላ ጸሎት፡ "መሓረነ አብ!"ን፡ ከቻሉ፡ በኹለት ወገን ኾነው፥ አለዚያ፡ በኅብረት፡ በዜማ፥ ጊዜ የሚያጥር ከኾነ ግን፡ በዜማና በንባብ፥ ወይም፡ በንባብ ብቻ ይበሉት፡፡
ቀጥሎ፡ ምንባብ፤ ለሦስቱ ዕለታት ከተመደቡት ምንባቦች መካከል፡ የዕለቱ፡ ከላይ፡ በ፪ኛው ተራ ቁጥር፥ በተራ ፊደል (ሐ.) ያለው ጥቅስ፡ በ፩ኛው ተራ ቁጥር በተመለከተው መሠረት፡ ይነበብ፡፡

፭ኛ፡ "አድኅነነ ሕዝበከ!"ን፡ በኅብረት ዜማ ይጸልዩት፡፡ ከዚያ አያይዘው፡ ካህን ካለ፡ የሠርክ ጸሎተ ኪዳንን ያድርሱ፡፡
ቀጥሎ፡ ምንባብ፤ ለሦስቱ ዕለታት ከተመደቡት ምንባቦች መካከል፡ የዕለቱ፡ ከላይ፡ በ፪ኛው ተራ ቁጥር፥ በተራ ፊደል (መ.) ያለው ጥቅስ፡ በ፩ኛው ተራ ቁጥር በተመለከተው መሠረት፡ ይነበብ፡፡

፮ኛ፡ "እግዚኦታ!"ን፡ "በእንተ ማርያም"ን ጨምሮ፡ በመቅደሳዊ ዜማ፡ ካህን ካለ፡ ሕዝቡ፡ ከእርሱ እየተቀበሉ፥ አለዚያ፡ በኹለት ወገን ኾነው እየተቀባበሉ፡ ይጸልዩት፡፡
ቀጥሎ፡ ምንባብ፤ ለሦስቱ ዕለታት ከተመደቡት ምንባቦች መካከል፡ የዕለቱ፡ ከላይ፡ በ፪ኛው ተራ ቁጥር፥ በተራ ፊደል (ሠ.) ያለው ጥቅስ፡ በ፩ኛው ተራ ቁጥር በተመለከተው መሠረት፡ ይነበብ፡፡

፯ኛ፡ የመዝጊያ ጸሎት፡-

ሀ. "እስእለኪ ማርያም፡ በሃሌ ሉያ!" በዜማ፤ ፫ ጊዜ፤
ለ. የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን መዝሙር፤ በዜማ፡፡
ሐ. "ኢትዮጵያ ሆይ! አገራችን፥ ረስቼሽ እንደኾን ቀኘ ትርሳኝ!"፤ በዜማ፤
መ. "አባታችን ሆይ!"፥ "እናታችን ሆይ!" መዝሙር፤ በዜማ፤
ሠ. የኢትዮጵያውያን፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር፤ በዜማ፤
ሠ. "ጸሎተ ስባሔ፡ ለእግዚአብሔር" እና "ጸሎተ ሱላሜ፡ ለማርያም" በንባብ፤
ረ. ካህን ካለ፡ ከእርሱ ኑዛዜ በኋላ፡ እየተባረኩ፥ አለዚያ፡ "የነቢያት፥ የሓዋርያት" የሚለውን የበረከት ጸሎት አብረው ብለው፡ መሰነባበት፡፡

## <u>የጸሎቱ መክፈቻ</u>

<u>በግእዝ፡-</u> "አአትብ ገጽየ፥ ወኵለንታየ፥ በትእምርተ መስቀል! በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፥ በቅድስት ሥላሴ፡ እንዘ አአምን፥ ወእትመኀፀን፤ እክሕደከ ሰይጣን! በቅድመ ዛቲ፡ እምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ እንተ ይእቲ፡ ስምዕየ ማርያም ጽዮን፤ ለዓለም ዓለም፡፡"

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u> "ፊቴንና ኹለንተናዬን በመስቀል ምልክት እያማተብሁ፡ ልዩ በኾነች ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡ በአብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ስም አምኘና ተማጽኘ፡ እናቴና መጠጊያዬ፥ ምስክሬና ቤተ ክርስቲያኔ በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ፊት፡ አንተን ሰይጣንን ክጄሃለሁ! ለዘለዓለሙ፡፡"

# <u>ጸሎተ ሃይማኖት፡ ዘኢትዮጵያውያን፡፡</u>

<u>በግእዝ፡-</u> ንሕነ ኢትዮጵያውያን፡-

ነአምን፡ በአሐዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብ፡ አኀዜ ኵሉ፥ ገባሬ ሰማያት ወምድር፡ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ፡፡

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልደ አብ ዋህድ፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ብርሃን ዘእምብርሃን፥ አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን፤ ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ፤ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ፡፡

ዘበእንቲአነ ለሰብእ፥ ወበእንተ መድኃኒትነ፡ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ ወተሠገወ፡ በግብረ መንፈስ ቅዱስ፡ እማርያም እምቅድስት ድንግል፤ በነሢአ ሥጋ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ እምነፍሳ፡ ኮነ ብእሴ ፍጹመ፡፡ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፥ ወሓመ፥ ወሞተ፤ ወተቀብረ በእንቲአነ፡፡ ወተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት፡፡ ዐርገ በስብሓት ውስተ ሰማያት፡፡ ወነበረ በየማነ አቡሁ፥ በመንበሩ ዘበዕሪና፡፡ ዳግመ ይመጽእ በስብሓት፤ ይኰንን ሕያዋነ ወእሙታነ፡፡ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡፡

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡፡ ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ፥ ማኅየዊ ዘበአማን፥ ዘሠረጸ እምአብ፥ ዘንሰግድ ሎቱ ወንሰብሖ፡ ምስለ አብ ወወልድ፥ ወዘነበበ በነቢያት፥ ዘወረደ ላዕለ ሓዋርያት፥ ወጺጋሁ ዘመልዓ ዓለም፡ በቤዛ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምጥንት፥ በኪዳነ ልቦና ዘአበው ቀደምት፥ ወዘአጽንዓት በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ በላዕለ ኵሉ ጉባዔ ዘሓዋርያት፡፡ በውስቴታ ያቀርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ ለኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፡ ጺጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ፡፡

ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፥ ለሥርየተ ኃጢአት፡፡

ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወተ ዘይመጽእ፡፡ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን፡፡

## <u>ጸሎተ ኪዳነ ቃል፡ ዘኢትዮጵያውያን፡፡</u>

ንሕነ ኢትዮጵያውያን፡-

ነአምን በኢትዮጵያውናን፡ ዘኪዳን ቅዱስ፥ ህልው በዓቂበ ቃላት ኪዳናውያት፥ እለ ወህቦሙ እግዚአብሔር፡ ለውሉደ ሰብእ፡፡

አምላክነ፡ ሣረረ ገዘ ቱ ሰብእና ኢትዮጵያዊ፡ በኪዳነ ልቦና፡ በዘኮነ እምሥርዓተ ከብካብ፡ ዘአዳም ወሔዋን፡ በዘመነ አበው ቀዳማዊ፤ ወመትሎሁ፡ አዕረጎ ለዝ ሕንፃ፡ በቀስተ ደመናሁ ለኖኅ፥ ወበቍርባኑ ዘመልከ ጼዴቅ፥ ወበግዝረቱ፡ ዘአብርሃም፤ ወበዘመነ ሕግ ማእከላይ፡ ነደቆ ማኅፈዱ፡ በጽላተ ሙሴ፥ ወበመንበረ ዳዊት፡ ዘግህደ በፅምረተ አሥራወ ዘርየሙ ለንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያዊት፥ ወለንጉሥ ሰሎሞን እሥራኤላዊ፡ ከመ ያስተሰነአዎ ኵለንታሁ፡ በኪዳነ አሪት፤ ወእምድኅረ አጽንዖቱሰ፡ በሥጋሁ ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ፡ ዘተወልደ እምድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት እምዛቲ ሥርው ምልዕት፡ አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡ በፍጻሜ ዘመን ዘሕይወት፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡፡ በእንተዝ፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኀቤሁ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሠረ ተዋሕዶ፡፡

ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ "ክርስቲያን"፡ በስመ ዚአሁ፡ ዘተብህለ "ክርስቶስ"፡ ነአምን፡ ከመ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ካህንነ ወንጉሥነ ዘለዓለም፡ በሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፡ ዘአስተርአየ በመዋዕል ቀዳማዊ፡ ወዘኮነ አርአያሁ ለክርስቶስ፡ በልደቱ፡ ዘኮነ፡ እምትሥልስተ ዘርዕ፡ ዘእምአንጋደ ሴም፥ ወካም፥ ወያፌት፡፡

ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ "ኢትዮጵያውያን" በስመ ዚአሃ ዘተብህለት "ኢትዮጵያ"፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ድንግል ማርያም፡ እመ ሕያዋን አማናዊት፥ ወታቦተ ጽዮን ዘለዓለማዊት፥ ወንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ በዘወሊዶታ ለአምላክ፡፡

ነአምን፡ በቀስተ ደመና፡ ዘተሠርገወ በሠለስቱ ዓበይት ኅብረ ቀለማት፡ ዘውእቶሙ ሐመልሚል፥ ወወርቀ፥ ወቀይሕ፡ ዘተውህበ ለነ እምእግዚአብሔር፡ እንተ በኀበ ኖኅ፡ ከመ ውእቱ ይኩነነ፡ ትእምርተ ኪዳን ዘለዓለም፡፡

ነአምን፡ በማኅተምነ ዘለዓለም፡ ዘረከብነ እምአምላክነ፡ ወበዘውእቱ ዘተነግረ በእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መፈጽም ለኪዳኑ ቅዱስ፡ በዝ ቱ ቃል ዘመለኮት፡ እንዘ ይብል፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"፥ ወበቃለ ትንቢት፡ ዘተነግረ፡ በእንተ ማርያም ድንግል፡ እንዘ ይብል፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር"።

ነአምን፡ ከመ ንሕነ፡ ወራስያነ መንግሥቱ ወላእካኒሁ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ወልድናነ፡ በዘውእቱ ዘተከለልነ በክብረ ልደት እምእግዚአብሔር በመንፈስ፡ እንበይነ ጸጋሁ ዘኪዳኑ ቅዱስ።

ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ እንበለ ፅርዓት፡ ለሥርየተ ኃጢኣት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ፡ ለአጽንዖተ ዝ ቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ።

ነአምን፡ ከመ ውእቱ ሃይማኖትነ ዘኢትዮጵያውና፡ ገሃደ ይወጽእ፥ ወቅድስናሁ ይትአወቅ፡ በምግባሪነ ዘኢትዮጵያውና፡ ዘንፈጽም በተዋሕዶተ ፍቅርነ ለኢየሱስ ክርስቶስ፥ ወለድንግል ማርያም።

ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሓፈ ኢትዮጵያውናነ ዘኪዳን ቅዱስ፡ በልቦናነ፥ ወመሀረነ፥ ወረሰየነ፡ ንዕቀብ በሀልዎትነ በእንተ ቃለ ኪዳኑ። ለዓለም ዓለም፤ አሜን።

## <u>የኢትዮጵያውያን፡ የሃይማኖት ጸሎት።</u>

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

እኛ ኢትዮጵያውያን፡-

ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ በእርሱ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ ሥጋ፥ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡ ፍጹም ሰው ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረው፥ በሐዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

በሙታን ትንሣኤ፥ በሚመጣውም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፥ አሜን።

# የኢትዮጵያውያን፡ የቃል ኪዳን ጸሎት::

እኛ ኢትዮጵያውያን፡-

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች፡ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን::

አምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ በመጀመሪያው የአበው ዘመን፡ በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤ ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቁርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሐረጎች በማዋሐድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው:: ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የ ረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን::

እርሱ፡ “ክርስቶስ” ተብሎ፡ እኛን “ክርስቲያን” ያሰኘን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን::

እርሷ “ኢትዮጵያ” ተብላ፡ እኛን “ኢትዮጵያውያን” ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕያዋን እናትና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን::

አረንጓዴ ብጫ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን::

የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው፡ “ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ” የሚለው፡ መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር” የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን::

በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ፡ የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን::

ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢአታችንን ዘወትር፡ በንስሓ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን::

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ኾነን በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን::

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን:: ለዘለዓለሙ፤ አሜን::

# THE ETHIOPIAN CREED

**በእንግሊዝኛ፡-**

We Ethiopians believe in One God, God the Father, Almighty who possesses all, Maker of the Heavens and Earth, the visible and the invisible.

We believe in God the Son, Jesus Christ, One Lord, the only begotten Son of the Father, who was with Him before the creation of the world. He is Light from Light, True God from True God, begotten not made, and, in His Divine Essence, one with His Father. All things were made by Him, and without Him nothing whatsoever was made, in Heavens or on Earth.

He came down from Heavens for our sake, for the sake of humanity, for our salvation. He was Incarnate in the womb of the Virgin Mary by the Divine Work of the Holy Spirit, and, acquiring the human soul and the human flesh from Her, became the Perfect Man.

In the days of Pontius Pilate, He suffered, was crucified, died and was buried for our sake. And He rose from the dead on the third day, ascended in glory into Heaven and sat on His Throne at the right-hand of His Father.

He will come again in glory to judge the living and the dead. There is no end to His Kingdom.

We believe in God the Holy Spirit. He is the life-giving Spirit who proceeds from God the Father, spoke through the Prophets, and, by the atonement of Jesus Christ, descended upon the Apostles and filled the world with His Grace. We worship and glorify Him with the Father and the Son.

We believe in the One Church of The Holy Covenant that was founded by the Word of God, Jesus Christ, initially in the Hearts of the Patriarchs, and later sustained by His Divine Messages through the Prophets, and finally brought to perfection through the Holy Spirit by His convocation of the Apostles, and where His Body and Blood is offered as Sacrifice for the Holy Communion with God, and where the Sacramental Blessings of the Holy Spirit are bestowed upon and communicated to all believers.

We believe in One Baptism for the remission of sins.

We believe in the Resurrection from the dead and the Life to come, world without end. Amen.

# THE TESTIMONIAL<br>OF THE ETHIOPIANS ON THE HOLY COVENANT

We Ethiopians believe in our Ethiopianhood of the Holy Covenant that embodied and conserved the Seven Divine Covenants the Lord granted to humanity.

Our God, in the Era of the Genesis, founded the Ethiopian Entity on the Covenant of the Soul, through the Matrimony of Adam and Eve.

Then in the Patriarchal period, He raised it, through Noah's Rainbow, Melchizedek's Offering and Abraham's Circumcision, to the next stage of its eschatological growth.

In the transitional Era of the Old Testament, He structured it, through Mose's Ark and David's Throne, to the finishing level that caused to bring about, under the Covenant of the Law, the genealogical union of the Ethiopian Queen Makkedda and the Israelite King Solomon.

Finally, in the Era of the Everlasting Life, He brought it to completion with the Sacrificial Body and Blood of His Son Jesus Christ, born of the Virgin Mary, who is the pure seed descended from that preordained genealogical union, thus culminating the Ethiopian Entity with the Eternal Crown of the Covenant of the Holy Spirit.

We believe that Ethiopia, as such, represents the Kingdom of God on Earth constituting the three Houses of the People, of the Administration and of the Priesthood achieved through such progressive development in Her uninterrupted existence under the protection and guidance of the Holy Covenant.

We believe that Jesus Christ who is the Son of God and in the name of whom we are called Christians and who is born of the seed that sprung from Shem, Ham and Japhet, in the Ethiopian image of nationhood, ordination and kingship of His precursor, Melchizedek, is our Eternal Priest and King.

We believe that the Mother of God, the Virgin Mary, who is the True Mother of the Living and the Eternal Ark of the Covenant, is the personification of Ethiopia, our Queen in Heavens and on Earth and in whose name we are called Ethiopians.

We believe that the tri-coloured banner of Green, Yellow and Red, symbolizing the sign of the Rainbow, is our Eternal National Flag entrusted to us by God through Noah.

We believe that the Divine Word of *"the Conquering Lion of the Tribe of Judah"* is ascribed to Jesus Christ who is the ultimate manifestation of the Holy Covenant, and the Prophetic Word of *"Ethiopia Stretches out Her Hands to God"* is attributed to the Virgin Mary, and that both Words of the Holy Spirit are our Eternal Divine Seal we received from Our God as a Nation of The Holy Covenant.

We believe that our spiritual birth from God, through the Grace of the Holy Baptism of The Covenant, entitled us to be heirs and servants of the Kingdom of God.

We believe that, in order for us to maintain such Divine birthright privilege, to confirm our inheritance of God's Kingdom and to continue rendering our pertinent services, it is our constant commitment to absolve our sins through incessant repentance and partake the Holy Communion of Our Lord Jesus Christ.

We believe that the genuine manifestation and the distinctive identification of our Faith in the Ethiopianhood of The Holy Covenant are best demonstrated by the typical Ethiopian deed that we perform in consideration and reflection of our love for both Jesus Christ and the Virgin Mary.

We believe that it is our God who, in accordance with His Word of The Covenant, inscribed in our hearts, taught us and made us to preserve in our lives this Ethiopianhood, which is the embodiment of the Holy Covenant. Amen.

## ሰላም ለኪ

በግእዝ፡-

ሰላም ለኪ! እንዘ ንሰግድ ንብለኪ! ማርያም እምነ! ናስተበቍዓኪ÷ እምዐርዌ ነዓዊ፡ ተማሕፀነ ብኪ፤ በእንተ ሐና እምኪ፤ ወኢያቄም እምአቡኪ፤ ማኅበረነ ዮም፤ ድንግል ባርኪ!

በኢትዮጵያኛ፡-

እናታችን ማርያም ሆይ! "ሰላም ላንቺ ይኹን!" እያልን፡ እንሰግድልሻለን! እንማልድሻለንም! ከክፉው አውሬ፡ ከዲያብሎስ ታድኚን ዘንድ ተማፅነንብሻል! ድንግል ሆይ! ስለእናትሽ፡ ስለሐና÷ ስለአባትሽ ስለኢያቄምም ብለሽ፡ ማኅበራችንን፡ ዛሬ ባርኪልን!

## ጸሎተ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ

በግእዝ፡-

ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር፤ ወትትሐሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ ወመድኃኒየ፤ እስመ ርእየ ሕማማ ለዓመቱ፡፡ ናሁ እምይእዜሰ÷ ያስተበፅዑኒ÷ ኵሉ ትውልድ፤ እስመ ገብረ ሊተ÷ ኃይለ ዓቢያተ፡፡ ወቅዱስ ስሙ፡፡ ወሣህሉኒ፡ ለትውልደ ትውልድ÷ ለእለ ይፈርኅዎ፡፡ ወገብረ ኃይለ በመዝራዕቱ፤ ወዘርዖሙ፡ ለእለ የዓብዩ ሕሊና ልቦሙ፤ ወነሠቶሙ ለኃያላን፡ እመናብርቲሆሙ፡፡ አዕበዮሙ፡ ለትሑታን፤ ወአጽገቦሙ፡ እምበረከቱ ለርኁባን፡፡ ወፈነወ ዕራቆሙ ለብዑላን፡፡ ወተወክፎ ለእሥራኤል ቍልዔሁ፤ ወተዘከረ ሣህሎ፡ ዘይቤሎሙ፤ ለአበዊነ÷ ለአብርሃም፤ ወለዘርዑ፤ እስከለዓለም፡፡

በኢትዮጵያኛ፡-

በአዲሱ ኪዳን፡ የምሥራች ቃል፡ "ማርያምም አለች" የሚለውን፡ ያንቺን ጸሎት፡ እናቀርብልሽ ዘንድ፡ እመቤታችን ድንግል ሆይ! ፍቀጂልን! "ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን በታላቅ ክብር ታመሰግነዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ እጅግ ደስ ይላታል፤ የእኔን የአገልጋዩን ፈተናና መከራ አይቷልና፡፡ እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ "ብፅዕት!" ይሉኛል፤ እርሱ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና፡፡ ስሙ፡ ቅዱስ ነው፡፡ እርሱን በሚፈሩት ዘንድ፡ ምሕረቱ፡ ለልጅ ልጅ ይኖራል፡፡ ታላላቅ ሥራዎቹን፡ በክንዱ ያደርጋል፡፡ በእውቀታቸው የታበዩትን፡ በታተናቸው! በኃይላቸው የተመኩትን፡ ከሥልጣናቸው አወረዳቸው! የተዋረዱትንም፡ ከፍ ከፍ አደረጋቸው! የተራቡትን፡ ከበረከቱ አጠገባቸው! በሀብታቸው የታመኑትን፡ ዕርቃናቸውን ሰደዳቸው! ብላቴናውን እሥራኤልን ተቀበለ፤ ለአባቶቻችን÷ ለአብርሃምና ለዘሩም፡ እስከዘለዓለም የገባውን፡ የቃል ኪዳን ምሕረቱን አስታወሰ፡፡"

## አቡነ ዘበሰማያት!

በግእዝ፡-

አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ÷ በከመ በሰማይ÷ ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ÷ ዘለለዕለትነ÷ ሀበነ ዮም፤ ሕድግ ለነ÷ አበሳነ÷ ወጌጋየነ÷ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ፡ ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ÷ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት÷ ኃይል ወስብሐት፤ ለዓለመ ዓለም!

በኢትዮጵያኛ፡-

አባታችን ሆይ! በሰማያት የምትኖር! ስምህ ይቀደስ! መንግሥትህ ትምጣ! ፈቃድህ፡ በሰማይ እንደኾነች፡ እንዲሁ፡ በምድር ትኹን! የዕለት እንጀራችንን፡ ስጠን ለዛሬ! በደላችንንም፡ ይቅር በለን! እኛም፡ የበደሉንን፡ ይቅር እንደምንል፤ አቤቱ! ወደፈተና አታግባን! ከክፉ ኹሉ፡ አድነን እንጂ፡፡ መንግሥት ያንተ ናትና÷ ኃይል÷ ምስጋና፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

## ጸሎተ ንሥሓ:- ሦስቱ ስደተኞች፡ በባቢሎን እሳት መከከል የጸለዩት፡፡

የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ክበር፥ ተመስገን! ስምህ ለዘለዓለም፡ የተመሰገነና የከበረ ነው፡፡ ባመጣህብን መከራ ኹሉ፡ አንተ፡ እውነተኛ ነህ፤ ሥራህ ኹሉ፡ የታመነ፥ ሥርዓትህም ኹሉ፡ የቀና ነው፤ ፍርድህም ኹሉ እውነት ነው፡፡ በተቀደሰችው በአባቶቻችን አገር፡ በኢትዮጵያ፡ መልካሙን ኹሉ፡ በትክክለኛው ጻኝነትህ አድርገህልን ነበር፡፡ እኛ ግን፡ አንተን ትተን፡ እጅግ ስለበደልን፡ ከዚህ ኃጢአታችን የተነሣ፡ በእውነተኛው ፍርድህ፡ ይህን ኹሉ መከራ አመጣህብን፡፡ በኹሉ በደልን፤ ትእዛዝህንም አልሰማንም፡፡ ለእኛ፡ መልካም ይኾንልን ዘንድ፡ ያዘዝኸ ፥ የሰጠኸንንም፡ ቃል ኪዳንህን ጠብቀን፡ አልፈጸምንም፡፡ ያመጣህብንንና ያደረግህብንን መከራ ኹሉ፡ በእውነተኛ ፍርድህ አደረግህብን፡፡ በአንተ ፈጽመው በማያምኑ፡ ኃጢኣተኞችና ወንጀለኞች በኾኑ ጠላቶቻችን እጅ አሳልፈህ ሰጠኸን! በምድር ላይ ካለ ዓመፀኛና ክፉ ከኾነ ሰው ኹሉ በባሱ መሪዎችም እጅ ጣልኸን!

አኹንም፡ ለእኛ፡ ለምንፈራህ አገልጋዮችህ፡ የገዛ ሥራችን፡ ኃፍረትንና ጉስቊልናን ስላመጣብን፡ 'እንዲህ ኾንን!' ብለን፡ አቤቱታችንን፡ ወደአንተ ልናሰማ፡ የሚገባን አይደለም፤ ብቻ፡ በስምህ ስለተጠራን፡ ስለስምህ ስትል፡ ለባሰ መከራ፡ አሳልፈህ አትስጠን! ቃል ኪዳንህን አትለውጥብን! የቃል ኪዳን ምሕረትህንም፡ ከእኛ አታርቅ!'

በዚህ ዘመን፡ አለቃም የለም፤ ነቢይም የለም፤ ንጉሥም የለም፤ ቊርባንም የለም፤ መሥዋዕትም የለም፤ ጽንሓ ይዞ፡ ጸሎተ ዕጣን የሚደግምና የሚያጥን ካህንም የለም፤ ምእመናን፡ በፊትህ፡ የሃይማኖት ጸሎታቸውን አቅርበው፡ ከአንተ ይቅርታንና ምሕረትን የሚያገኙበት ቤተ መቅደስና አገርም የለም፤ ስለዚህ፡ ቀድሞ፡ የላሞችንና የጊደሮችን፥ የሰቡ፡ የብዙ በጎችንም መሥዋዕት እንደተቀበልህ፡ ዛሬም፡ የዋህ በኾነችና የትሕትና መንፈስን በተመላች የግል ሰውነታችን የምናቀርብልህን መሥዋዕታችንን፡ በፊትህ እንደዚያ አድርገህ ተቀበልልን! በአንተ ያመኑና የተማመኑ፡ (ኢትዮጵያውያን) ኹሉ እንዳያፍሩ፡፡

## የምሕላው ጸሎት

### ምስባክ፤ *(ኹለቱንም እጆች ዘርግቶ)*

**በግእዝ:-**

*ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤ ነገሥተ ምድር ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር፤ ወዘምሩ ለአምላክነ፡፡*

**በኢትዮጵያኛ:-**

*ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች፤ የምድር መንግሥታት፡ እግዚአብሔርን አመስግኑ! ለአምላካችንም ዘምሩ!*

### ሕዝባዊው እግዚኦታ

*(በሕዝባዊ ዜማ)*

| በግእዝ:- | በኢትዮጵያኛ:- |
|---|---|
| እግዚኦ፡ መሓረነ ክርስቶስ፤ | አቤቱ! ክርስቶስ ሆይ! ማረን! |
| በእንተ ማርያም፡ መሓረነ ክርስቶስ፤ | ክርስቶስ ሆይ! ስለማርያም፡ ማረን! |
| ኪራላይሶን፤ | አቤቱ! ይቅር በለን! |
| ኦ አምላክ፤ | አምላክ ሆይ! |
| እግዚኦ ክርስቶስ፤ | አቤቱ! ክርስቶስ ሆይ! |
| ያድኅነነ እመዓቱ፤ ይሠውረነ በምሕረቱ፡ | ስለወለደችው፡ ስለማርያም፡ ከቊጣው |
| በእንተ ማርያም ወላዲቱ፤ | ያድነን! በምሕረቱ ይሠውረን! |
| ስምዓነ አምላክነ፡ ወመድኃኒነ! | አምላካችን መድኃኒታችን ሆይ! ስማን! |

...፳፫

## *<u>ሃሌ ሉያ፤ መሓረነ አብ!</u>*

*(በዜማ፡ በኅብረት ሊያዜሙት ይቻላል፡፡)*

<u>በግእዝ፡-</u>

*ሃሌ ሉያ! ዘበእንቲኣሃ ለቤተ ክርስቲያን፡ ተጸፋህከ በውስተ ዓውድ፡ ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር፤ ዘበእንቲኣሃ፡ ዝግሓታተ መዋቅሕት ፆረ፤ ወተዓገሠ ምራቀ ርኩሰ፥ እንዘ አልቦ ዘአበሰ፤ አምላክ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሰቅለ፡፡*

*(በኹለት ወገን ኾነውና በየአራቱ ነጥቦች ላይ አቁመው እየተቀባበሉ፡ በዜማ ሊሉት ይቻላል፡፡)*

*መሓረነ አብ፡፡ ሃሌ ሉያ፡፡ ተሣሃለነ ወልድ፡፡ ሃሌ ሉያ፡፡ መንፈስ ቅዱስ መሓሪ፡ ተዘከረነ በሣህልከ፡፡ (፫ ጊዜ ይበሉት!)*

*ለከ ንፌኑ ስብሓተ፤ ወለከ ናዓርግ አኰቴተ፡፡ መሓረነ መሓሪ፡ ኃጢኣተነ አስተሥሪ፡፡ ወአድኅነነ፡፡ ወተማኅፀን ነፍሰነ ወሥጋነ፡፡ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፡፡ አምላክነ፡፡ ወመድኃኒነ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሣሃለነ፡፡ በብዝኃ ምሕረትከ፡፡ ደምስስ አበሳነ፡፡ ወፈኑ ሣህለከ ላዕሌነ፡፡ እስመ እምኀቤከ፡፡ ውእቱ ሣህል፡፡ ሃሌ ሉያ መሓረነ አብ መሓሪ፡፡ ወተሣሃለነ፡፡ ሀብ ሣህለከ መሓሪ፡፡ ኢታጥፍአነ፡ ተዘኪረከ ዘትካት፡፡ በምሕረትከ፡፡ እስመ መሓሪ አንተ፡፡ ወብዙኅ ሣህልከ ለኵሎሙ እለ ይጼውዑከ፡፡ ይጼውዑከ በጽድቅ፡፡ ሰማዒ ወትረ፡፡ ከሃሊ ዘውስተ አድኅኖ፡፡ ከሃሊ፡፡ ዘውስተ አድኅኖ፡፡ ለአምላክነ እስመ ጽድቅ ቃሉ፡፡ ንስኣሎ ለአብ፡፡ ይፈኑ ለነ ሣህሎ፡፡ እስመ አብ የአክል ለዘሰኣሎ፡፡*

*ሃሌ ሉያ፡፡ ስብሓት ሎቱ ይደሉ፡፡ ሃሌ ሉያ፡ አኰቴት ሎቱ ይደሉ፡፡ ሃሌ ሉያ፡፡ ለክርስቶስ ለእግዚኣ ኵሉ፡፡ ሃሌ ሉያ፡ ሃሌ፡ ሃሌ ሉያ፡፡ ወይእዜኒ፡፡ መኑ ተስፋየ፡፡ አኮኑ፡፡ እግዚአብሔር፡፡ ውስተ እዴከ እግዚኦ አመሓፅን ነፍስየ፡፡ ኀበ አምላከ ምሕረት፡፡ አምሓፅን ነፍስየ፡፡ ኀበ ንጉሠ ስብሓት፡፡ አመሓፅን ነፍስየ፡፡ በእግዚእየ ወአምላኪየ፡፡ አመሓፅን ነፍስየ፡፡ እምኵሉ ምግባረ እኩይ፡ አድኅና ለነፍስየ፡፡ ሀቡ፡፡ ንስኣሎ፡፡ ንስኣሎ፡፡ ናስተምሕሮ፡፡ ለአምላክነ ጻድቅ እስመ ጽድቅ ቃሉ፡፡*

*ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰዓኖ፡፡ አምላከ ነዳያን ረዳኤ ምንዱባን፡፡ ንሕነ ኀቤከ ተማኅፀነ፡፡ ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰዓኖ፡፡ አምላከ ነዳያን ናዛዜ ኅዙናን፡፡ ንሕነ ኀቤከ ተማኅፀነ፡፡ ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰዓኖ፡፡ አምላከ ነዳያን ወተስፋ ቅቡጻን፡፡ ንሕነ ኀቤከ ተማኅፀነ፡፡ ወበከመ ዐቀብከነ እምነግህ እስከ ሠርክ፡፡ ዕቀበነ እግዝኦ እምሠርክ እስከነግህ፡፡*

*(በኅብረት የሚቀጥሉት)*

*ተሣሃልከ እግዚኦ ምድረከ፤ ሃሌ ሉያ፤ ስማዕ ጸሎተነ፡ ወስእለተነ፤ ወስረይ ኵሎ ኃጢኣተነ፤ ስማዕ፤ ጸሎተነ፤ ወስእለተነ፤ ዘሰማዕኮ ጸሎቶ ወስእለቶ ለእዝራ፤ ተወከፍ ምሕላነ፤ ሰላመከ ሀበነ፤ ወእማዕከሌነ ኢትርኀቅ፡፡*

*ወሚጥ መዓተከ እምኔነ፤ ሃሌ ሉያ! ንዒ ኀቤየ እንቲአየ፤ ሠናይት ርግብየ፤ መዓዛ አፉሃ ከመ ኮል፡ ወኵሉ ነገራ በሰላም፡፡*

*አርእየነ እግዚኦ ሣህልከ፤ ሃሌ ሉያ! ሰላመ አብ፤ ወሰላመ ወልድ፤ ወሰላመ መንፈስ ቅዱስ፤ የሃሉ ማዕከሌክሙ አኀው፡፡*

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

*ሃሌ ሉያ! (ሀለወ፥ ህልው፥ ይሂሉ፡፡ የነበርህ! ያለህ! የምትኖር!) ለቤተ ክርስቲያን ስትል፡ በአደባባይ በጥፊ የተመታህ፥ አቤቱ! ይህን ማድረግህ፡ እርሷን፡ በከበረ ደምህ፡ ትቀድሳት ዘንድ ነው፡፡ ለእርሷ ሲል፡ ታሥሮ መጐተትን የተቀበለ፥ የፈጸመውም በደል ሳይኖር፡ ርኩስ ምራቅን የታገሠ አምላክ፡ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ፡፡*

*አብ ሆይ! ማረን! ሃሌ ሉያ! ወልድ ሆይ! ይቅር በለን! ሃሌ ሉያ! መሓሪ መንፈስ ቅዱስ ሆይ! በይቅርታህ አስበን! (፫ ጊዜ)*

*ለአንተ፡ ፍጹም ምስጋናን እናቀርባለን፡፡ ቸር፥ ይቅር ባይ ሆይ! ማረን! ኃጢኣታችንንም አስተሥርይልን! የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! አድነን! በነፍስ በሥጋም ጠብቀን! አምላካችን፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ይቅር በለን! በቸርነትህ ብዛት በደላችንን ደምስስ! ይቅርታህንም ላክልን! ይቅርታ ካንተ ዘንድ ነውና፡፡*

ሃሌ ሉያ! ይቅር ባይ አብ ሆይ! ማረን! ይቅር በለን! መሐሪ የኾንህ አቤቱ! ይቅርታህን ስጠን! የቀድሞ ኃጢኣታችንንም አስበህ አታጥፋን! በቸርነትህ፡ አንተ ይቅር ባይ ነህና፡፡ ለሚጠሩህ፥ ለሚለምኑህ ኹሉ፡ ይቅርታህ ብዙ ነው፡፡ በእውነት ይጠሩሃል፤ አንተም ዘወትር ትሰማለህ፡፡ ኹሉን ለማድረግ የምትችል ነህ፡፡ ኹሉን ለማድረግ የሚችል የአምላካችን ቃሉ እውነት ነውና፡፡ ይቅርታውን ይልክልን ዘንድ፡ አብን እንለምነው! አብ፡ ለለመነው ኹሉ ይበቃልና፡፡

ሃሌ ሉያ! ለእርሱ ምስጋና ይገባል፡፡ ሃሌ ሉያ፡ ከእርሱ ክብር ምስጋና ይገባል፡፡ ሃሌ ሉያ፡ ለኹሉ ጌታ፡ ለክርስቶስ ምስጋና ይገባል፡፡ ሃሌ ሉያ! ሃሌ፥ ሃሌ ሉያ!

ዛሬስ፡ ተስፋዬ ማነው? እግዚአብሔር አይደለምን? አቤቱ! ነፍሴን፡ ለአንተ አደራ አስጠብቃለሁ፤ ከምሕረት አምላክ ዘንድ፡ ነፍሴን አደራ አስጠብቃለሁ፤ በጌታዬና በአምላኬ፡ ነፍሴን አደራ አስጠብቃለሁ፡፡ ከክፉ ሥራ ኹሉ፡ ነፍሴን፥ ሰውነቴን አድናት!

ኑ! እንለምነው! እንለምነው! እንማልደው! የአምላካችን ቃሉ፡ እውነት ነውና፡፡

ኹሉን የሚችል፥ የሚሳነውም የሌለ፥ የድሆች አምላክ! የተቸገሩትን የሚረዳ! አቤቱ! እኛም ወደአንተ ተማጥነናል! ኹሉን የሚችል፥ የሚሳነውም የሌለ፥ የድሆች አምላክ! ያዘኑትን የሚያጽናና! አቤቱ! እኛም ወደአንተ ተማጥነናል! ኹሉን የሚችል፥ የሚሳነውም የሌለ፥ የድሆች አምላክ! ተስፋ ለቈረጡ ተስፋቸው! አቤቱ! እኛም ወደአንተ ተማጥነናል!

ከጧት እስከማታ እንደጠበቅኸን፥ አቤቱ! እንዲሁ፡ ከማታ እስከጧት ጠብቀን!

*(በኅብረት የሚቀጥሉት፡-)*

ሃሌ ሉያ! ጌታ ሆይ! ለፍጥረትህ ቸርነትህን አድርግ! ጸሎታችንንና ልመናችንን ስማ! ኃጢኣታችንንም ኹሉ ይቅር በል! የዕዝራን፡ ጸሎቱንና ልመናውን እንደሰማህ፡ የእኛንም ጸሎትና ልመና ስማ! ምሕላችንን ተቀበል! ሰላምህን ስጠን! ከመካከላችንም አትራቅ!

ሃሌ ሉያ! መዓትህን ከእኛ መልስ! የአፏ መዓዛ እንደኮል፥ ነገርዋ ኹሉ ሰላማዊ የኾነ፥ የኔዪቱ መልካም ርግብ ማርያም ሆይ! ወደእኔ ነዪልኝ!

ሃሌ ሉያ! አቤቱ! ቸርነትህን አሳየ ! የአብ ሰላም፥ የወልድ ሰላም፥ የመንፈስ ቅዱስ ሰላም፡ በመካከላችን ይኹን!

## <u>አድኅነነ ሕዝበከ</u>

*(በኅብረት ኾነው፡ በዜማ ሊሉት ይቻላል፡፡)*

<u>በግእዝ፡-</u>

አድኅነነ ሕዝበከ፤ ወባርከነ ርስተከ፤ ሀበነ፡ ኃይለ ወመዊአ ለአግብርቲከ፥ ለእለ ንኄውዕ ስመከ፤ ዕቀበነ ውሉደ ሕዝብከ፤ ወሕፀረነ፡ በኃይለ መላእክቲከ፡ ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት፤ በኃይለ መስቀልከ፡ ርድአነ፥ በዕፀ መስቀልከ ቤዝወነ፡፡

በእንተ አብርሃም ፍቁርከ፤ ወበእንተ ይስሐቅ ቍልዔከ፤ ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ፤ ተዘከር እግዚኦ ኪዳነከ! ፍጡነ ፈኑ ሣህለከ! መሐር ኪያነ ዘፈጠርከ! ሥረይ፡ ኃጢአተ ሕዝብከ! ወመሐር ተግባረከ! እግዚኦ፡ ታጥፍአነ ሓሰ ለከ!

በእንተ ማርያም ወላዲትከ፤ ወበእንተ ዮሐንስ መጥምቅከ፤ ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳኒከ፤ ርድአነ ወትረ፡ በኃይለ መስቀልከ፤ ኢታስተኃፍረነ እግዚኦ በቅድሜከ፡፡

እግዝእትነ! ነጽሪ ኀቤነ! ጸልዪ ለነ ለደቂቅኪ! ወአድኅንነ እምኵሉ ምንዳቤ ወኀዘን! መዓልተ ምስሌነ፤ ወሌሊተ ማዕከሌነ፤ አንተ እግዚኦ! ኢትርኀቅ እምኔነ! ሀሉ ምስሌነ! ረዳኤ ኵነነ! ኢትግድፈነ ወኢትመንነ አምላከ ሰላም ተራድአነ!

ኢትግድፈነ! ኢትግድፈነ ወኢትመንነ አምላከ ሰላም ተራድአነ! *(፫ ጊዜ)*

እግዝእትነ! እግዝእትነ! ነጽሪ ኀቤነ! ሰላመ ወልድኪ፡ የሀሉ ምስሌነ! *(፫ ጊዜ)*

እግዚኦ! መሐረነ ክርስቶስ! *(፫ ጊዜ)*

*(አንገታቸውን ዝቅ በማድረግ፡ ይህን የምስጋና ቃል፡ በኅብረት ዜማ ያሰሙ!)*

ስብሓት ለእግዚአብሔር፡ ኪያነ ዘፈጠረ፡ ከመ ናምልኮ!
ስብሓት ለማርያም፡ እመ አምላክ፡ ንግሥትነ፤ ወእምነ!
ስብሓት ለመስቀለ ክርስቶስ፡ ዕፀ መድኃኒት፤ ኃይልነ፤ ወጸወንነ!

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

የቃል ኪዳን ሕዝብህ የኾንነውን፡ እኛን ወገኖችህን አድነን! ባርከንም! ስምህን ለምንጠራ፡ ለእኛ ለአገልጋዮችህ፡ ድል መንሣትንና ኃይልን ስጠን! የቃል ኪዳን ሕዝብህ ልጆች ነንና ጠብቀን! በመስቀልህ ታዳጊነት እርዳን! በመስቀልህ ተቤዠን!

ስለባለሟልህ አብርሃም፥ ስለወዳጅህ ይስሓቅ፥ ስለመረጥኸው እስራኤልም ብለህ፡ አቤቱ፥ ቃል ኪዳንህን አስብ! ይቅርታህን ፈጥነህ ላክ! የፈጠርኸን እኛን ማረን! የወገኖችህን ኃጢአት አስተሥርይ! የእጅህን ፍጥረቶች እኛን ማረን! አቤቱ፥ አታጥፋን! ይህ በአንተ ዘንድ አይደረግ!

ስለእናትህ፡ ድንግል ማርያም ብለህ! ስለአጠመቀህ፡ ዮሓንስና ስለቅዱሳንህ ኹሉ ብለህ፡ ኹልጊዜ በመስቀልህ ታዳጊነት እርዳን! አቤቱ፥ በፊትህ አታሳፍረን!

እመቤታችን፥ እናታችን ሆይ!! ወደእኛ ተመልከቺ! ለእኛ ለልጆችሽ ለምኚልን! ከችግርና ከኀዘን ኹሉ አድኚን!

አቤቱ፥ ቀን፡ ከእኛ ጋር፥ ሌትም፡ በመካከላችን ኹን! አንተ፡ ከእኛ አትለይ! ከእኛ ጋር ኑር! ረዳትም ኹነን! አትተወን! አትናቀንም! የሰላም አምላክ ሆይ፥ ተራዳን!

አትተወን፥ አትተወን፥ አትናቀንም! የሰላም አምላክ ሆይ፥ ተራዳን! ፫ ጊዜ

እመቤታችን ሆይ፥ እመቤታችን ሆይ! ወደእኛ ተመልከቺ! የልጅሽም ሰላም፡ በእኛ ላይ አድሮ ይኑር! ፫ ጊዜ

አቤቱ፥ ክርስቶስ ማረን! ፫ ጊዜ

*(አንገታቸውን ዝቅ በማድረግ፡ ይህን የምስጋና ቃል፡ በኅብረት ዜማ ያሰሙ፡፡)*

እርሱን እናመልከው ዘንድ፡ እኛን ለፈጠረ እግዚአብሔር፡ ምስጋና ይገባል፡፡
አምላክን ለወለደች፡ ለንግሥታችንና እናታችን፡ ድንግል ማርያም ምስጋና ይገባል፡፡
ኃይልና ጋሻ፥ መድኃኒትም ለኾነን፡ ለክርስቶስ መሰቀል፡ ምስጋና ይገባል፡፡

## <u>የእግዚአታ ጸሎት</u>

*(ካህኑ፡ ከፍ ባለ ድምፅ፡ እንዲህ የሚለውን መግቢያ፡ በንባብ ያሰማ፡-)*

<u>በግእዝ፡-</u>

ሰላመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ወፍቅራ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ፤ ሞገሰ መስቀሉ፥ ወህብተ ረድኤቱ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ኢይርኃቅ ወትረ፡ እማዕከሌየ ወእማዕከሌክሙ እስከለዓለም!

*(ቀጥሎ፡ ከሕዝቡ ጋር ፫፥ ፫ ጊዜያት በመቀባበል፡ መጀመሪያ በንዑስ ዜማ፥ ከዚያ፡ በልዑል ዜማ፡ ይህን ይበል!)*

እግዚኦ መሓረነ ክርስቶስ!

*(ኢያይዞም፡ ከሕዝቡ ጋር ፫፥ ፫ ጊዜያት በመቀባበል፡ መጀመሪያ፡ በልዑል ዜማ፥ ቀጥሎ፡ በንዑስ የመዝጊያ ዜማ፡ ይህን ተከታይ የምሕላ ጸሎት ይበል!)*

በእንተ ማርያም መሓረነ ክርስቶስ!

*(በመጨረሻ፡ ኹሉም፡ በኅብረት፡ ይህን ያዚሙ!)*

ሰአሊ ለነ ማርያም፡ ምሕረተ ወልድኪ የሐውጸነ እምአርያም፡፡ ሰአሊ ለነ ማርያም ለለሰዓቱ÷ ተግባረ እደዊሁ፡ ለወልድኪ ኢንጥፉዕ በከንቱ፡፡ ኵሎ መዓልተ÷ ወኵሎ ሌሊተ÷ ብዙኀ ኃጢኣተ ዘገበርነ፤ በእንተ ማርያም፡ እምከ÷ መሓሪ ስረይ ለነ!

እግዚኦ÷ ዕቀበነ፡ ለኵልነ ኢትዮጵያውያን፡ ውሉድ÷ ወአዋልድ፡ ዘኪዳንከ ቅዱስ!

እግዚኦ÷ ዕቀባ፡ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ!

እግዚኦ÷ ዕቀቦሙ፡ ለኵሎሙ ሕዝበ ኢትዮጵያ!

እግዚኦ÷ ዕቀቦሙ፡ ለኵሎሙ ሕዝበ ዓለም፡ እለ ይትመሓፀኑ በስምከ ቅዱስ÷ ወበስማ ለእምነ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወላዲተ አምላክ!

እግዚኦ÷ ፈውሶሙ፡ ለአግብርቲከ÷ ወለአዕማቲከ ኵሎሙ ኢትዮጵያውያን፡፡

እግዚኦ÷ አዕርፎሙ፡ ለነፍሳተ አግብርቲከ ወለአዕማቲከ ኵሎሙ ኢትዮጵያውያን!

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

*(ካህኑ፡ ይህን የእግዚኦታ መግቢያ ጸሎት፡ ከፍ ባለ የ ባብ ድምፅ ያሰማ!)*

የአብ÷ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሰላም÷ አምላክን የወለደች፡ የእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ፍቅር÷ የአምላካችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመስቀሉ ሞገስና የጸጋው ረድዔት፡ ምንጊዜም፡ በእናንተም÷ በእኔም ይደር! ለዘለዓለሙ!

*(ኢያይዞም፡ ከሕዝቡ ጋር ፫÷ ፫ ጊዜያት በመቀባበል፡ መጀመሪያ በንዑስ ዜማ፡ ቀጥሎ፡ በልዑል ዜማ፡ ይህን ይበል!)*

"አቤቱ! ክርስቶስ ማረን!"

*(ቀጥሎ፡ ከሕዝቡ ጋር ፫÷ ፫ ጊዜያት በመቀባበል፡ መጀመሪያ፡ በልዑል ዜማ÷ ከዚያ፡ በንዑስ የመዝጊያ ዜማ፡ ይህን ተከታይ የምሕላ ጸሎት ይበል!)*

"ስለማርያም ብለህ÷ ክርስቶስ ማረን!"

*(በመጨረሻ፡ ኹሉም በኅብረት፡ ይህን ያዚሙ!)*

ማርያም ሆይ÷ የልጅሽ ምሕረት፡ ከአርያም ይጐበኘን ዘንድ ለምኚልን! ማርያም ሆይ÷ የልጅሽ የእጁ ሥራዎች የኾንነው እኛ፡ ከንቱ ኾነን እንዳንጠፋ፡ በየሰዓቱ ለምኚልን! በቀንም÷ በሌሊትም፡ የሠራነውን፡ ብዙውን ኃጢኣታችንን ኹሉ፡ ስለእናትህ፡ ድንግል ማርያም ብለህ፡ መሓሪው አምላክ ሆይ÷ ይቅር በለን!

ጌታ ሆይ÷ የቅዱሱ ኪዳን ወንዶችና ሴቶች ልጆችህ የኾንነውን፡ እኛን ኢትዮጵያውያንን፡ በያለንበት ጠብቀን!

ጌታ ሆይ÷ አገራችንን ኢትዮጵያን ጠብቅልን!

ጌታ ሆይ÷ በኢትዮጵያ የሚኖሩትን ሕዝቦች ኹሉ ጠብቅ!

ጌታ ሆይ÷ በቅዱስ ስምህ÷ በወለደችህ እናታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም ስም የተማፀኑትን የዓለም ሕዝቦች ኹሉ ጠብቅ!

ጌታ ሆይ! በልዩ ልዩ ሕመም÷ ችግርና መከራ ላይ የሚገኙትን ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮችህን ኢትዮጵያውያንን፡ በረድዔትህና በምሕረትህ ጐብኝልን!

ጌታ ሆይ÷ በዕረፍተ ሥጋ የተለዩንን፡ የወንዶችና የሴቶች አገልጋዮችህን ኢትዮጵያውያንን ነፍሳት በገነት ሕይወት አሳርፍልን!

# የምሕላው ጸሎት መዝጊያ

## <u>እስእለኪ ማርያም በሃሌ ሉያ!</u>

*(በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን፡ ኢትዮጵያውያን፡ በግራኝ አሕመድ ወረራ ጊዜ የጸለዩት።)*

<u>በግእዝ፡-</u>

በእንተ ፍቅረ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኬንያ፤
እስእለኪ ማርያም በሃሌ ሉያ!
ኀዘና ስምዒ ወብካያ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ።

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

ሠሪዋ በኾነው፡ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ኾነሽ፥
ማርያም ሆይ! በሃሌ ሉያ፡ የምስጋና ቃል የምንለምንሽ፥
አገራችንን ኢትዮጵያን፡ ኀዘኗንና ለቅሶዋን ሰምተሽ፥
እንድታማልጂ ነው ከልጅሽ።

## <u>የኢትዮጵያውያን፡ የቅዱሱ ኪዳን መዝሙር</u>

፩. ሃሌ ሉያ ለአብ፡ ለሰማይ አባታችን፤
ስብሐት ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ካህን ንጉሣችን፤
ለመንፈስ ቅዱስም፡ ጸጋ ሕይወታችን፤
አቅርበናልና፡ በዝርጉ እጃችን፤
ጌታ ሆይ ተቀበል፡ ይኸው ምስጋናችን፤ ይኸው ምስጋናችን።

፪. ሰላም ለማርያም፡ ጽዮን እናታችን፤
ኪዳነ ምሕረት፡ ድንግል ንግሥታችን፤
ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ቤተ ክርስቲያናችን፤
ርስትሽ ነንና፡ በሕዝብነታችን፤
ይሰማ በአርያም፡ ይኸ መዝሙራችን፤ ይኸ መዝሙራችን።

፫. ለሰውነታችን፡ ለመንፈስ ምግባችን፤
ለሕመም መድኃኒት፡ ለደዌ ፈውሳችን፤
ከክፋት፥ ከኃጢአት፥ ከሞት መዳኛችን፤
በመከራ ጊዜ፡ ተስፋ መጽናኛችን፤
በእምነትና ምግባር፡ የትእግሥት ፍሬአችን፤ የትእግሥት ፍሬአችን።

፬. ለግል፥ ለቤተሰብ፥ ለኅብረት ኑሮአችን፤
ለአንድነት፥ ለፍቅር፥ ለሰላም ግባችን፤
ለሰብአዊ መብት፥ ለፍትሕ ዋስትናችን፤
አጥቂ እንዳይጎዳን፡ አለኝታ ጋሻችን፤
ለድል አድራጊነት፡ መሣሪያ ኃይላችን፤ መሣሪያ ኃይላችን።

፭. ለዚህ ፊደላችን፡ ለግእዝ ቋንቋችን፤
ለእውቀት፥ ለጥበብ፥ ለሥልጣኔአችን፤
ለልማት፥ ለዕድገት፡ መሠረት ሕንፃችን፤
በተፈጥሮ ውበት፡ ገነት አገራችን፤
የምንኖርበት፡ የታሪክ ክብራችን፤ የታሪክ ክብራችን።

፮. ለኖኅ ልጆች ውኅደት፡ የዘር ሓረጋችን፤
ለኢትዮጵያዊነት፡ መጠሪያ ስማችን፤
ለማንነታችን፡ ልዩ ማስረጃችን፤
በቀስተ ደመና፡ ነጻነት ልብሳችን፤
የማርያም መቀነት፡ ሰንደቅ ዓላማችን፤ ሰንደቅ ዓላማችን።

፯. አንበሳው ክርስቶስ፡ ምልክት አርማችን፣
ካምላክ ያገኘነው፡ ሕገ መንግሥታችን፣
ማንም የማይነጥቀን፡ የሰማይ ወርቃችን፣
የምንጠብቀው፡ ያደራ ውርሳችን፣
ቅዱሱ ኪዳን ነው፡ ሕያዉ ቅርሳችን፥ ሕያዉ ቅርሳችን።

## <u>የኢትዮጵያውያን፡ የመከራ ጊዜ መዝሙር</u>

ኢትዮጵያ ሆይ፥ ሀገራችን! ረስቼሽ እንደኾን፡ ቀኜ ትርሳኝ፣
ያላሰብሁሽ እንደኾን፡ መላሴ ትናጋዬን ሰልቶ ይውጋኝ፣
ከደስታዬ ኹሉ በላይ፡ ኢትዮጵያ ሆይ! አንቺ ባትኾኝ፡ ስደት ይብላኝ።
አቤቱ ፈጣሪያችን፡ በኢትዮጵያ ቀን፡ ጠላቶቿን ኹሉ አስብ፣
አፍርሷት፡ ኢትዮጵያን፡ እስከመሠረቷ ድረስ፡ የሚሉትንም ሕዝብ።
እናንት ትምክህተኞች፡ የኢትዮጵያ ጸሮች፥ የተንኰላችሁን ብድራት፣
የሚመልስ ነው አምላካቸን፡ በፍትሕ በተአምራት፣
በሚጠሉሽ ላይ፡ በእውነት፥
በቅን ለሚፈርደው ንጉሥ፡ ምስጋናችን ይብዛለት።
ኢትዮጵያ ሆይ፥ ሀገራችን! ረስቼሽ እንደኾን፡ ቀኜ ትርሳኝ።

## <u>ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የምስጋና ጸሎት</u>

*(በመዝሙር)*

አባታችን ሆይ! የምትኖር በሰማይ፣
መንግሥትህ በስምህ፡ ሰፈነች በእኛ ላይ፥ ሰፈነች በእኛ ላይ።
በሰማይ የጸናች፡ ሕያው ፈቃድህ፣
ተፈጸመች በምድር፡ በሥግው ቃልህ፥ በሥግው ቃልህ።
ፍቅርህ ለምግባችን፡ ፍጥረትን ያስገኘች፣
በደልን ደምስሳ፡ ዕርቅን መሠረተች፣ ዕርቅን መሠረተች።
ጌታ ሆይ! አዳንከን፡ ከሞት ከፈተና፣
በልጅህ ቤዛነት፡ በትንሣኤው ፋና፥ በትንሣኤው ፋና።
ኃይልና ምስጋና፡ ጸንተው ለመንግሥትህ፣
አበቃኸን እኛን፡ ለቅዱስ ኪዳንህ፥ ለቅዱስ ኪዳንህ።

## <u>ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የሰላምታ ጸሎት</u>

*(በመዝሙር)*

እናታችን ሆይ! ማርያም ድንግል፥ ማርያም ድንግል፣
ሰላም እያልንሽ ነው፡ በገብርኤል ቃል፥ በመልአኩ ቃል።
በሥጋ አካልሽ፡ ደግሞም በኅሊና፥ ደግሞም በኅሊና፣
ባሕርይሽ ኾነ፡ ፍጹም ድንግልና፥ ፍጹም ድንግልና።
ላሸናፊው አምላክ፡ ለእግዚአብሔር እናት፥ ለጌታ እናት፣
ማቅረብ ይገባናል፡ ሰላምታን በምነት፥ ሰላምታን በውነት።
ከሴቶች መካከል፡ ባለሽ ቅድስና፥ ባለሽ ቅድስና፣
ማኅፀንሽ አፈራ፡ የሕይወትን መና፥ የሕይወትን መና።
ደስ ይበልሽ አንቺ፡ የግዜር ባለጸጋ፥ ያምላክ ባለጸጋ፣
አቅርቢን ከልጅሽ፡ ደሙ ኾኖን ዋጋ፣ ደሙ ኾኖን ዋጋ።

<u>የኢትዮጵያውያን፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር</u>

*(የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ፡ ከመካከላቸው፡ አንዱ፡ ከፊት ለፊታቸው ይዞ ይዘምሩት፡፡)*

ኢትዮጵያ ሆይ(ድንግል ማርያም)! ደስ ይበልሽ፤
　　　　　　በአምላክሽ ኃይል በንጉሥሽ(በኢየሱስ ክርስቶስ)፡፡
ተባብረዋልና ልጆችሽ(ኢትዮጵያውያን)፤
　　　　　　አይነካም ከቶ ነጻነትሽ፡፡
ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ፤
　　　　　　አትፈሪም ከጠላቶችሽ፡፡
የድል ሰንደቅ ዓላማችን፥
　　　　　　ይኑርልን ለክብራችን፡፡

<u>ጸሎተ ስባሔ ለእግዚአብሔር፡ እለ ያቀርቡ ሎቱ፡ ኢትዮጵያውያን፡፡</u>

<u>በግእዝ፡-</u>

ኦ አቡነ እግዚአብሔር! ንሴብሐከ፡ በእንተ ዘተወከፍከ ዝ ቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንዘ ይብል፡ "አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፡- 'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ፥ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ፥ ዘለለዕለትነ፥ ሀበነ ዮም፤ ሐድግ ለነ፥ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፥ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ፡ ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም!'" ወበእንተ፡ ዘአብዛኅከ ለነ፡ ኂሩትከ፤ ወዘገበርከ ለነ፡ ምሕረትከ፥ ወዘፈጸምከ ለነ፡ ፍቅርከ፥ ወዘወሀብከነ ጸጋከ፡ ለከዊነ ነፍስነ ወሥጋነ፡፡

ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ በምክንያተ ቤዛ ወልድከ መድኅን፡ ዘተወልደ እምቅድስት ድንግል ማርያም፡፡ በእንተዝ፡ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ፡ በምድር፥ አኮ በሰማይ ባሕቲቱ፡፡ ወዓዲ፡ ተቀደሰ ስምከ፡ በምድር፡፡ ወመጽአት መንግሥትከ፡፡ ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፥ ከማሁ፡ ኮነ፡ በምድርኒ፡፡

አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ ለመፍቅደ ኵሉ ህልዎትነ፥ ወአኮ ሲሳይ፡ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ፡፡ ወመጦከነ በኵሉ ጊዜ፡ ሥጋ ወልድከ ቅዱስ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ዘኮነ ለነ፡ መድኃኒት፥ ወምግበ ነፍስ፡ ዘይረስየነ ሕያዋን ዘለዓለም፤ ወበውእቱሰ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኵሎ ኃጢኣተነ፥ ወአበሳነ፡ ግሙራ፥ ወኢማእዜ፤ ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ፡፡

ወዐልዓልከነ በልደተ መንፈስ ቅዱስ ዘጥምቀት፥ ወጸጋ ዘንስሓ፡ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ፡፡

ወአውጻእከነ እመንሱት ዘዘዚአሁ፤ ወአድኃንከነ እምኵሉ እኩይ፤ ወሞዕከዎ ለዲያብሎስ፥ ወአሰሰልከ ለሞት፤ ወበእንተ ዝ ቱ፡ አሠለጥከነ ንሄሉ፡ በሕይወተ ትንሣኤከ፡፡

ኦ እግዚኦ! ንሴብሓከ ወትረ፡ በእንተ ኂሩትከ፥ ወምሕረትከ፥ ወፍቅርከ፥ ወጸጋከ፡ ዘአወፈይከነ፡ በዘኢይትከሃል ይትነገር መጠኑ፤ ወዓዲ፡ በእንተ ዘትሁበነ፡ ኵሎ ዘንፈቅድ፡ እንዘ አኮ ዘንሰአለከ፡፡

ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ፡ ትኴንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዘተብህለ፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"፤ እለ ንሄሉ ንሕነ፡ ይእዜ፡ በውስቴታ፡ ከመ ትትረአይ ወትሰፍን በገሃድ፡ በዝ ቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሤርዎሙ ለእከይ፥ ወለኃጢኣት፥ ወለሞት፡፡

እስመ ለከ፡ ኃይል፥ ወስብሓት፥ ወመንግሥት፤ ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለም ዓለም፤

አሜን፡፡

## ጸሎተ ሱላሜ፡ ለድንግል ማርያም፡ እለ ያቀርቡ ላቲ፡ ኢትዮጵያውያን፡፡

ኦ ማርያም እምነ! ንብለኪ፡ "ሰላም ለኪ!" በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ፡፡ ድንግል፡ በሕሊናኪ፤ ወድንግል፡ በሥጋኪ፡፡ ይደልወኪ ዝ ሱላሜ፤ እስመ ኮንኪ አንቲ፡ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት፡ በእንተ ዛቲ ንጽሓ ባሕርይኪ፡፡

አንቲ ውእቱ ሔዋን ቅድስት፥ ወቡርክት፡ እምኵሎን አንስት፡ በእንተ ዘአሥረፀ ማሕፀንኪ፡ ፍሬሁ ዘዕፀ ሕይወት፡ በዘውእቱ ኮነ አዳምሁ ቅዱሰ፡፡ ተፈሥሒ! ኦ ንግሥትነ፡ በሰማይ ወበምድር! እስመ ዘተወደስኪ ጥንት፡ በአፈ ነቢያት፡ እንዘ ይብሉኪ፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"፥ ወንሕነኒ፡ በዘሀልዎትነ፡ እንዘ ንብለኪ፡ "እምነ ጽዮን!"፡፡ ንዌድሰኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ ምልዕተ ጸጋ!"፡ እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ ድኅነትነ፡፡

ነአምን፡ ከመ ኢተግሕሠ ክመ እምኄነ፡ ማሕፅንተኪ፡ በአምጣነ እንተ ኢተግሕሠ፡ እምፍቁር ወልድኪ፤ እስመ አንቲ ውእቱ እምነ፡ ዘምሕፅና፥ ወንሕነ፡ ውሉድኪ፥ ወአዋልድኪ፡ ዘምሕፅና፡ በቃለ አማሕፅኖ ዘወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አምላክነ፥ ወመድኃኒነ፡፡

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ልዑል፡ አቡነ ኄር፡ በእንተ ዛቲ ኂሩቱ፡ ዘገብረት ለነ፡፡

ለዓለመ ዓለም፤ አሜን፡፡

## ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የምስጋና ጸሎት፡፡

<u>በኢትዮጵያኛ፡-</u>

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! *"እናንተ ስትጸልዩ፡ 'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ፥ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ፥ ዘለለዕለትነ፥ ሀበነ ዮም፤ ሕድግ ለነ፥ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፥ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ፡ ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም!' በሉ!"* ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትክልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምክልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን፡፡ ስለዚህ እናመሰግንሃለን፡፡

ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን፡፡ ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም የምትኖር ኾንህ፡፡ ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ፡፡ መንግሥትህም መጣችልን፡፡ በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም እንዲሁ ኾነ፡፡

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን፡፡ ለዘላለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን፡፡ በእርሱም፡ ኃጢኣታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን፡፡ እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን፡፡

የአንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የ ስሓን ጸጋ አደልኸን፡፡

ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፥ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን፡፡

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን፡፡

*"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* በተባለው፡ በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፥ ኃጢኣትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን፡፡

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም ያንተ ናቸው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የሰላምታ ጸሎት፡፡

እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ “ሰላም!” እንልሻለን፡፡ በአሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፡፡ በዚህ የ ጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡

ማሕፀንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ፡፡ ቀድሞ በነቢያት፡ “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር” የተባልሽ፥ እኛም፡ “እምነ ጽዮን” ስንልሽ የ ርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ፡፡

እግዚአብሔር አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳኑ ምሕረቱን ለዘለዓለም ፈጽሚልና፡ “ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ” እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን፡፡

በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንቺ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ፡ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም እንደማይለየ እናምናለን፡፡ ይህን ያደረገ፡ ቸሩ አባታችን፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፡፡ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

## PRAYER OF THE ETHIOPIANS IN GLORIFICATION OF THE LORD

Our Father God! We thank You, and glorify You for the prayer which Your Son Jesus Christ taught us to say, “*Our Father who art in Heaven, Hallowed be Your Name. Your Kingdom come. Your Will be done on Earth as it is in Heaven. Give us this day our daily bread. And forgive us our debts, as we forgive our debtors. And do not lead us into temptation; but deliver us from the evil one. For, Yours is The Kingdom, and The Power, and The Glory, forever. Amen.* ” and, through His atonement, for the answer You gave us to our supplication in that prayer.

You provided us with everything that pertains to our spiritual and material needs for the body as well as for the soul. Your generosity for us is bountiful; Your mercy, complete; Your love, perfect, and Your grace, overflowing.

Through the salvation of Your Son, born of the Holy Virgin Mary, the Grace of the Holy Spirit descended over and filled the whole world. Thus, today You reside not only in Heavens, but on Earth as well. Your Name is hallowed also on Earth. Your will that is done in Heavens is done also on Earth. Your Kingdom has come and is revealed on Earth.

By Your endowment of Nature, We recognized that You have arranged for our daily bread and for the entire life-long provisions of our bodily needs.

You gave us, on daily basis, the Holy Sacrament of the Body and Blood of Your Son as nourishment for our Soul, and as an assurance for our salvation and eternal life. Through the same Sacrament, You exonerated us completely from our sins and iniquities once for all, and empowered us to forgive the debts of our debtors.

For us to be Your Children, You granted us the exaltation of the spiritual birth of Baptism and the Sacrament of the Grace of Penance. You led us out of every temptation, delivered us from evil, and overthrew the powers of the Devil and Death that dominated our lives. Finally, You ordained for us the honour and the privilege to live in the Rapture of Your Resurrection.

O Lord! We are always grateful to You for Your inexpressible generosity, mercy, love and grace, as well as for all our needs that You provided us before we even ask You.

We wait for the time You promised us to come, when Your Kingdom of Truth, in which we are now blessed to live, under the Kingship of Jesus Christ, *"The Conquering Lion of the Tribe of Judah",* will prevail and destroy Evil, Sin and Death completely. Yes, we wait for the day when It actually reveals Itself to the material world and universally reigns over the whole realms of Creation.

Power, Glory and Kingdom are Yours, today as ever and forever, world without end. Amen.

## PRAYER OF THE ETHIOPIANS IN EXALTATION OF THE HOLY MOTHER.

Our Holy Mother Mary! With the Words of Greeting of the Angel Saint Gabriel, we bow to You in solemn salutation saying, "Hail, O Favoured One!" You are Virgin both in soul and in body. Because of Your perfect chastity, You became the Mother of the Almighty God. And so, You deserve such glorious salutation.

Your womb bore the Holy Adam who is the Sacred Fruit of the Tree of Life. Hence, You are the Holy Eve, the Chosen and the Blessed One among all the women.

In the early times, the Prophets spoke of You as *"Ethiopia stretches out Her Hands to God",* and we addressed you as 'Our Mother Zion'.

Rejoice, O Our Queen in Heavens and on Earth! God, through Your instrumentality fulfilled His promise of our Salvation and granted His Eternal Covenant of Mercy to His Creation. And so, we always praise You saying. "You are the Blessed, full of Grace."

In the Words of Jesus Christ, our Saviour, Priest and King, we are Your children, committed to Your Maternal guardianship; and You are our Holy Mother, entrusted to our spiritual dedication. Thus, we believe Your Motherhood that has never forsaken Your beloved Son will always be with us.

We thank Our Gracious Father, God the Most High, for His Benevolence of such magnitude. World without end, Amen.

## የመሰነባብቻ ቡራኬ

**የነቢያት የሓዋርያት የጻድቃን የሰማዕታት የቅዱሳን አበው የቅዱሳት አንስት፥ የትጉሃን መላእክት፥ የሊቃነ መላእክት፡ የቅዱስ ሚካኤል፥ የቅዱስ ገብርኤል፥ የቅዱስ ዑራኤል፥ የቅዱስ ሩፋኤል፥ የቅዱስ ራጉኤል፥ የቅዱስ ፋኑኤል፥ የቅዱሳን አርባዕቱ እንስሳ፡ ሱራፌል ወኪሩቤል፥ (የዕለቱ ቅዱስ) ረድኤትና በረከት፥ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የጌታችንና የመድኃኒታችን፥ የካህን፡ ሊቀ ካህናታችን፥ የ ጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የትስብእቱ፥ የልደቱ፥ የግዝረቱ፥ የበዓተ መቅደሱ፥ የስደቱ፥ የአገልግሎቱ፥ የጥምቀቱ፥ የፈተናው፥ የትምህርቱ፥ የተአምራቱ፤ የሕማማተ መስቀሉ፥ የሞቱ፥ የመቃብሩ፥ የትንሣኤው፥ የዕርገቱና የምጽአቱ ኃይልና ሞገስ፥ የእመቤታችንና የአገራችን፥ የሃይማኖታችንና የመቅደሳችን፥ የእናታችንና የ ግሥታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ምሕረት፥ የእግዚአብሔር አብ ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ወልድ ፍቅር፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድነት፡ ከኹላችንም ጋር ይኹን! አሜን፡፡**

+ + + + + + +